# የብሔርና የግለሰብ መብት ጥያቄ በኢትዮጵያ ትናንትናና ዛሬ

## ኅብረት፣ ኦፌዴን፣ ሶዴ ኃቅና አረና ትግራይ ፓርቲዎች በጋራ በታህሳስ 18ቀን 2001 ባዘጋጁት የውይይት መድረክ ላይ የቀረበ

በዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የቀረበ

አዲስ አበባ፣

1. መግቢያ

ኢትዮጵያ እኛ የዛሬው ትውልድ ከምንገምተው ውጭ ካልተበታተነች ወይም ከሌሎች አህጉሮች ጋር ተዋህዳ ቅርጽዋና ስምዋ ካልተለወጠ በስተቀር ሕያው ነች፡፡ በውስጥዋ 80 ሚሊዮን ያህል የምንሆን ኢትዮጵያዊ ዜጎች/ግለሰቦች አለን፡፡ በኢትዮጵያ ከ85 የማያንሱ ትላልቅና ትናንሽ የቋንቋ ማህበረሰቦች አሉ፡፡ በአስተዳደራዊ አወቃቀር አንፃር ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ስትሆን፣ ዘጠኝ የክልል ግዛቶች(States) እና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች አሉአት፡፡

በዛሬይቱ የኢትዮጵያ ግዛት (State) ጋር በተያያዘ አብዛኛው ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች የምንላቸው ማህበረሰቦች በ19ኛው መቶ ዓመት መጨረሻ አካባቢ በግዛቷ ተጠቃልለዋል፡፡ ይህችን በ19ኛው መቶ ዓመት መጨረሻ አካባቢ የተፈጠረችውን ዘመናዊ ኢትዮጵያ ለማስተዳደር የተቋቋመው ሰርዓት የአገሪትዋን ዜጎች የግለሰቦችና የብሔረሰቦችዋን መብቶችና አላከበሩም አላስከበሩም፡፡በማለት ስጀምር፣ የመብት ጥያቄም በዚህ ምክንያት መነሳቱን ለመግለጽ እፈልጋለሁ፡፡

የብሐረሰቦችና የግለሰቦች ሰብአዊ መብቶችም ባለማስከብራቸው የተነሳ የመብቶች ጥያቄ አመላላስ ላይ ብብዙ ምሁራን፣ በተለያዩ የፖለቲካ ሃይሎችና ግለሰቦች መሃከል ሰፊና ጥልቅ ክርክሮች ያለመግባባቶች ተከስተዋል፡፡ አሁንም እየተካሄዱ ናቸው፡፡ በነዚሁ መብቶች ጥያቄ ምክንያት ግጭቶች ነበሩ አሁንም አሉ፡፡ እነዚህ ግጭቶችም ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገሮችና ከአንዳንድ መንግሥት ጋር ባላት ግኑኝነቶች ላይ ተፅዕኖ ነበራቸው አሁንም አላቸው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በውስጥም በሕዝቦች መሃከል ያለመግባባቶችና ግጭቶች እየተከሰቱ በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ እልቂትና ውድመት እየደረሰ ነው፡፡ በሌላም በኩል ዜጎች ይታሠራሉ፣ ቶርች ይደረጋሉ፣ ይሰደዳሉ፣ ብዙዎች፣ የት እንደገቡም አይታወቅም ብዙዎችም ይገደላሉ፡፡

በመሆኑም የእነዚህ መብቶች ጥያቄዎች ባግባቡ ማለትም በፖለቲካ መልኩ መልስ ካላገኙ ችግሮች ከመቀጠል አልፈው መባባሳቸው አይቀሬ ነው፡፡የችግሮቹ መቀጠልና መባባስ ደግሞ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመጥት ይቻላል፡፡ ሠላምና መረጋጋት ማጣት ልማትና እድገት እንዳይኖርና የሕዝባችን

የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንዳይፈቱ ያደርጋል። ይህም ያገር ህልውና አደጋ ውስጥ መግባቱ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ጭካኔ የተሞላበት ብጥብጥና መተላለቅን ሊያስከትል ይችላል።

ስለሆነም የመብቶች ጥያቄዎቸ በተገቢው መንገድ ያለመፈታት ያስጨንቀናል። ጥያቄዎች ተገቢ መልስ የሚያገኙት እንዴትና በማን ነው የሚሉት ጥያቄዎች መመለስም ለመብቶቹ ጥያቄዎች መልስ የሚሆኑ አቅጣጫዎች ሊጠቁሙን ስለሚችሉ በነዚህ ጉዳዮች ላይ መወያየት አስፈላጊ ነው። ለዚህ ለምናካሔደው ውይይትም አስተዋፅዖ ሊያደርግ ይችል ይሆናል ብዬ በማመን ይህን ፅሑፍ አቅርቤአለሁ።

የፅሑፌ አወቃቀር መጀመሪያ ብሔርና ግለሰብ በሚሉ ቃላት ላይ ጥቂት አስተያየት ከሰጠ በኋላ በብሔርና ግለሰብ መብቶች ላይ ያሉትን የዓለም አቀፍና በመቀጠልም የብሔርና የግለሰብ መብቶች ጥያቄ አያያዝ በኢትዮጵያ የሚለውን ነጥብ ይዘረዝራል። ይህ ክፍል ታሪካችንን ባጭሩ ይዳስስና በዚህም ታሪክ ሂደት የተነሱት ሥርዓቶችና በእነዚህም ሥርዓቶች ዘመን የብሔርና የግለሰቦች መብት ጥያቄ አያያዝ ምን ይመስል እንደነበርና ምን እንደሚመስል ይዳስሳል። በመጨረሻም የመፍትሔ ሃሳቦች ሊሆኑ ይችላሉ ብዬ የማስበውን አቀርባለሁ።

## 2. የብሔርና የግለሰብ መብት ጥያቄ ምንነት

### 2.1. የብሔርና የግለሰብ ምንነት

ብሔር ማለት በአንድ የተወሰነ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ወይም ግለሰቦች የፈጠሩት ማህበረሰብ ነው። የዚህ ማህበረሰብ አባላት ከአንድ የጋራ ቅድመ አባት ወይም እናት የተወለዱ፣ ወይም እንወለዳለን ብለው የሚያምኑ ናቸው። የማህበረሰቡ አባላት የጋራ ቋንቋ ይናገራሉ። የጋራ ባህልና ልምድ አላቸው። የራሳቸው ታሪክ ሂደት ውስጥ ያለፉና እርስ በርሳቸውም ስሜታዊ ወይም ስነልቦናዊ ቁርኝት አላቸው። ማህበረሰቦቹ የራሳችን ነው ብለው የሚያምኑት አካባቢ ሲኖራቸው፣ አባላቱ የሚተዳደሩበትና ከውጭ ጣልቃገብነት የሚከላከሉበት ሰርዓት ኖሮአቸው ከሌላ አካል የተለዩና ያለ ሌላ ጣልቃገብነት የራሳቸው ማንነትና ሉዓላዊነት ጠብቀው የሚኖሩ ያላቸው የግለሰቦች ሰብሰብ ናቸው። በዓለም ታሪክ ውስጥ የዚህ ዓይነት ማህበረሰቦች በሌሎች ማህበረሰቦች ተውጠው ማንነታቸውና ህልውናቸው ከነጭራሹ የጠፋባቸው ሁኔታዎች አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ሉዓላዊነታቸውን አጥተው ነገር ግን የማንነታቸውን (ቋንቋ፣ ባህል፣ ሃይማኖት) መግለጫ ሳያጡ በሌላ ግዛት አስተዳደር ስር የኖሩና የሚኖሩም አሉ። በሌላ ሁኔታ ደግሞ ማንነታቸውንና ሉዓላዊነታቸውን አስጠብቀው የዘለቁም አሉ። እነዚህ ብሔረሰቦች የሚከበሩላቸው መብቶችና ማክበር ያለባቸው ግዴታዎች አሉ።

ብሔር የግለሰቦች ስብሰብ ነው፡፡ ግለሰብ በዚህ ዓይነት ሰብስብ ውስጥ ከሌሎች ግለሰቦች ጋር በወል ይኖራል፡፡ ግልሰቡ መብቶችና ግዴታዎችን በወል ይጋራል፣ ሆኖም ግን በተናጠል እንደ አንድ ሰው ከሌላ ጋር የማይጋራ የራሱ የግል ማንነትም አለው፡፤ በመሆኑም ሊከበሩለት የሚገቡ የግል መብቶች አሉት፣ በአንፃሩም ከሌሎች ጋር በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ግንኙነት ፈጥሮ በጋራ ስለሚኖር እሱም ማክበር ያለበት ግዴታ ይኖራል፡፡

አንድ ግለሰብ ሰብዓዊ ፍጡር እንደመሆኑ መጠን በግል፣ በራሱ ነፃ አስተሳሰብና እምነት በገዛ ሥልጣኑ በሃላፊነት እና ተጠያቂነት የራሱን ህይወት የሚመራበት ሁኔታ የመፍጠር እድል፣ ብቃትና ችሎታ አለው፡፡ ይህም ሆኖ አንድ ግለሰብ ከሌሎች ተነጥሎ ለመኖር አይችልም፡፡ ከጥቃትም ራሱን ለመከላከልና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት ማህበረሰቡን ይፈልጋል፡፡

ስለሆነም ግለሰብ የራሱን መብትና ማንነት እያስከበረ ማህበረሰቡ ከሱ የሚፈልገውን ግዴታ እየተወጣ ይኖራል፡፡

ይህን የግለሰብና የማህበረሰብ (ተናጠል/ወል) ግኑኝነትን በተመለከተ ሁለት ዓይነት አስተሳሰቦች ወይም ፍልስፍናዎች ነበሩ፡፡ አሁንም አሉ አንደኛው አስተሳሰብና አመለካከት ትኩረት የሚሰጠው ለግለሰቦችና ለግለሰብ መብቶች ነው፡፡ ይህ ፍልስፍና ለግለሰብ ፍጹም ነፃነት ይከራከራል፡፡ ግለሰቡ የሚኖርበት ማህበረሰብ ወይም ያንን ማህበረሰብ የሚያስተዳድር አገዛዝ በግለሰቡ ጉዳይ ውስጥ ፍጹም መግባት የለበትም ይላል፡፡ በተቃራኒው ግለሰብ የወል(collective) አካል እንደመሆኑ መጠን ለማህበረሰቡ ፍላጎት/ፈቃድ (will) መገዛት አለበት እንጅ ለአንድ ሰው ተለይቶ የሚታይ ማንነትና መብት የለም የሚል ክርክርም አለ ይላል፡፡ በዚህ አስተሳሰብ መሰረት ተፈጻሚ የሚሆነው የማህበረሰቡ የወል(collective) ፍላጎትና ፈቃድ ብቻ ነው፡፡ በዚህ አስተሳሰብ መሠረት አንድ ግለሰብ የህብረተሰቡን ወይም እሱን ለሚወክል ቡደን(ፓርቲ) ፍላጎት ፍፁም ተገዢ መሆን እንዳለበት፣ በዚህ አይነት ሁኔታ ለሚሰጥ ውሳኔ ይግባኝ ማለት እንደማይቻል፣ ህብረተሰቡ ወይም ወኪሉ የሚለውን የማይቀበል ራሱን ከህብረተሰቡ እንደነጠለ ከሃዲ የሚቆጠርና ሕዝባዊ ሽብር (ቅጣት) ሊወሰድበት እንደሚችል ይከራከራል፡፡ (እነዚህን ሁለት አይነት አመለካከቶች ወይም ሀሳቦች በተመለከተ የእነ J. Locke, Ronseau እና Jacobns ፍልስፍና ማየት ይጠቅማል):: የብሔረተኛነት የአብዮታዊና የኮሚኒስቶች እንቅስቃሴዎች ይህን የወል አካሄድ (Collectivism) አቀንቃኝነት ይንፀባረቅባቸዋል፡፡

### 2.2 የብሔርና የግለሰብ መብቶች ይዘት

#### 2.2.1 ሰነዶች

የግለሰብ መብቶችን በተመለከተ ምን እንሆነ መታየት ያለባቸው ዋና ዋና የሰብዓዊ መብቶች የስምምነት ድንጋጌ ሰነዶች ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

1. የ1945 (እኤአ) ዓ.ም የተባበሩት መንግስሥት ቻርተር
2. የ1948(እ.ኤ.አ) Universal Declaration Human Rights
3. የ1960 (እ.ኤ.አ) ዓ.ም UN General Assembly( Declaration 1514 (xv11))
4. የ1966 (እ.ኤ.አ) ዓ.ም International Convention on Civil and Political Rights.
5. የ1970 (እ.ኤ.አ) ዓ.ም Principles of International Law Concerning Friendly Relation and Cooperation Among States (UN- Declaration 2625, Xxv).
6. የ1976 (እ.ኤ.አ) International Convention on Civil and Political Rights.
7. የ1976 (እ.ኤ.አ) International Convention on Economic, Social and Cultural Rights
8. የ1981 (እ.ኤ.አ) ዓ.ም - African Charter on Human and Peoples Rights

#### 2.2.2 የግለሰብ መብቶች

የግለሰብ መብቶችን በተመለከተ የድንጋጌዎቹን ይዘት በአራት መክፈል ይቻላል፡፡

**1ኛ ፡- የግለሰቦች ተፈጥሮአዊ መብቶች**

እነዚህ መሠረታዊ የግለሰብ መብቶች ማንም ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካሉና የአእምሮ ጤንነቱ መጠበቅ፣ የሰብዓዊ ክብሩ መጠበቅ (dignity) በባርነት ያለመያዝ፣ በግብታዊ

መንገድ ያለመያዝ፣ ያለመታሠር፣ ለቶርች ያለመጋለጥ፣ በራስ ላይ ያለመመስከር፣ ለመናዘዝ ያለመገደድ፣ ከኢሰብአዊ አያያዝ ራስን መከላከል የሚሉትን መብቶች ያካትታሉ፡፡

**2ኛ፡- የዜጎች መብቶችና የፖለቲካ ነፃነት**

የዜጎች መብቶችና የፖለቲካ ነፃነቶች ውስጥ የሚካተቱት ግለሰቦች በነፃነት የማሰብ፣ ሃሳብ እምነትንና አመለካካትን በነፃነት የመያዝ፣ መረጃን የማግኘትና ሃሳብንና መረጃን በነፃነት ማስተላለፍ ፣ ዓላማንና ፍላጎትን ለማሳካት ከሌሎች ጋር ተሰባስቦ መወያየት፣ መመካከር፣ ትክክለኛ የሆነውን ነገር መደገፍና ትክክል ያልመሰለውን መቃወም ይህንንም በሰላማዊ ሰልፍና ማመልከቻ በማቅረብ መግለጽ፣ ▪ዓላማንና ፍላጎትን ከግብ ለማድረስ ከሌሎች ጋር በነፃነት መደራጀት ፣ ከሚቀርቡለት አማራጮች በሃከል የፈለገውን በነፃነት መምረጥ፣ ራስንም ሆነ የራስን ሃሳብ በነፃነት ለምርጫ ማቅረብ፣ የራስን የግል ጉዳይ ያለሌላ አካል ጣልቃ ገብነት በራስ መወሰን ይህም ማለት የራስን ጉዳይ በራስ ሃላፊነትና ተጠያቂነት መወሰን፣ የራስን የኑሮ ፍልስፍና መያዝ፣ የራስን ማህበራዊ ግንኙነት መፍጠር፣ በራስ ንብረት ላይ የመወሰንና በፈለገው ሁኔታ መተለም፣ ማደበር፣ ማቀናጀትና በሚጠቅመው መንገድ ማመቻቸት፣በአንድ ጉዳይ ላይ በራስ አስተሳሰብ በራስ መወሰን፣ ውሳኔውንም ተግባራዊ ማድረግ፣ ለዚህም የማስፈፀሚያ ደንቦች ፣መስፈርቶች ላይ ራስ መወሰን፣ ነፃ ሆኖ የራስን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ባህላዊ ህይወት (ኑሮ) እና አቋም (status) ላይ በራስ መወሰን ናቸው፡፡ የፈለገውን ቋንቋ፣ ምናገርን የፈለገውን ባህል የመከተል መብቶችም በዚህ ክፍል ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

**3ኛ. የእኩልነት መብቶች**

ግለሰቦች በሕግ ፊት እኩል መሆናቸው፣ በሕግም ሥር እኩል ጥበቃና ፍትሕ ማግኘት እንዳለባቸው የራስን የፈጣሪነት ችሎታ ለማዳበር እኩል እድል ማግኘት መብቶች የሚሉት በዚህ ነጥብ ሥር ይካተታሉ፡፡

**4ኛ. ማሕበረ ኪኮኖሚያዊ መብቶች**

ማህበረ ኢኮኖሚያዊ የግለሰቦች መብትን በተመለከተ

ሀ/ የግል ንብረት ባለቤትነት፣

ለ/ ከጋራ አየአገር ሀብትና አገልግሎቶች በፍትሃዊ መንገድ መቋደስ (መካፈል)

ሐ/ ማህበራዊ ዋስትና ማግኘት የሚሉት መብቶች ይጠቀሳሉ፡፡

### 2.2.3 የብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብቶች

በተዘረዘሩት ሰነዶች ውስጥ የብሔር ብሔረሰብ ሕዝቦች መብቶች ቢጠቀሱም ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ናቸው፡፡

1ኛ. ሁሉም ሕዝቦች እኩል መሆናቸው፣ እኩል ክብር ሊኖራቸው እንደሚገባና፣ እኩል መብቶች እንዳላቸው፣

2ኛ. ሕዝቦች የየራሳቸው አካባቢ /Territory/ ሊኖራቸው እንደሚችል፣ የራሳቸውን ህልውናና ማንነት ተጠብቀውላቸው የመኖር መብት እንዳላቸው

3ኛ. ሁሉም ሕዝቦች የየራሳቸውን ዕድል ያለሌላ ጣልቃገብነት በራስ የመወሰን መብት እንዳላቸውና ይህም ከጥያቄ ውስጥ የማይገባና የማይገረሰስ መብት እንደሆነ በዚህም መሠረት ሕዝቦች የራሳቸውን ፖለቲካዊ አቋም /Status/ በራስ የመወሰን፣ የራስን ውስጣዊ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና፣ ባሕላዊ እንዲሁም ስለሚጠቀሙበት ቋንቋ በራስ የመወሰንና እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ የራስን ፖሊሲ መተለምና ተግባራዊ የማድረግ መብት እንዳላቸው፣

4/ የኢኮኖሚያዊ፣ ባሕላዊና ፖለቲካዊ ጭቆና ያለበት ሕዝብ ከጭቆና ለመላቀቅና ነፃ ለመውጣት መብት እንዳለውና ይህንንም ትግል በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ዕውቅና ባላቸው ስልቶች ማካሔድ እንደሚችል፣ መንግሥታትም አንድ ሕዝብ ከዚህ ዓይነት ጭቆና ነፃ ለመውጣት የሚያደርገውን ትግል የመደገፍ ግዴታ እንዳለባቸው፣

ከነዚህም በተጨማሪ ሌሎች በዓለም ማህበረሰብ ዕውቅና ያገኙ መብቶችም አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/ ሕዝቦች ቋንቋቸው የመንግሥት ዕውቅና አግኝቶ የመንግሥት የሥራ ቋንቋ እንዲሆን የመጠየቅ መብት፣ በመንግስት ወጪም በቋንቋቸው ትምህርት የማግኘት መብት፣

ለ/ አንድ ሕዝብ ከጭቆና ለመላቀቅና መብቶቹን ለማስከበር የመደራጀት መብት፣ ተደራጅቶም በመንግሥት ውስጥ ፍትሃዊ መንገድ የመሳተፍ መብት

ሐ/ ከጋራ ሃብትና አገልግሎት በፍትሃዊ አኳኋን የመቋደስ (የመካፈል) መብት /Distribution Justice/

መ/ ከዚህ በፊት ኢ-ፍትሃዊ አያያዝ የደረሰበትና የተበዘበዘ ሕዝብ - የማካካሻ ጥያቄ የማንሳት /Recto factory/ Justice )መብት፣

## 3. የብሔርና የግለሰብ መብት ጥያቄ በኢትዮጵያ ትናንትና ዛሬ

### 3.1 መግቢያ

የአንድ ሕዝብ ወይም ብሔር እንዲሁም የግለሰቦች መብቶች ሲጣሱ የመብት ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀርም፡፡ አንድ የራሱን ማንነትና ነፃነት የነበረው አካል ግለሰብ ወይም የግለሰቦች ስብስብ (ማለትም ብሔር ሊሆን ይችላል፡፡) በፈቃዱ ሳይሆን በግዳጅ በሌላ አካል የበላይነት ሥር ከወደቀና፣ ተገዢ ሆኖ እንዲቀጥል በተለያዩ መንገዶች ወይም መሣሪያዎች /Mechanisms/ ሲገደድ፣ የኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካ መድልዎና ጭቆና ሲፈፀመበት፣ እንዲሁም መብቱንና ነፃነቱን ለማስከበር በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ይህን እንዳያደርግ የመከልከያና የቅጣት እርምጃ ሲወሰድበት የዚያ የአካል መብቱ ተጥሶአል እንላለን፡፡ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር የመብት ጥያቄ ይነሳል፡፡

በዚህ ክፍል የዚህ ዓይነት ሁኔታ በኢትዮጵያ ነበረ ወይ? አሁንስ አለ ወይ? የሚለውን ባጭሩ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡ ይህንንም ለማድረግ መጀመሪያ ያለፈውን ታሪካችንን ነካ ነካ ማድረግ ያስፈልገኛል፡፡

### 3.2 ቅድመ 19ኛው መቶ ዓመት ሁኔታ

#### 3.2.1 የኢትዮጵያ ህዝቦችን በተመለከተ፣

በቅርቡ ይፋ የሆነው የ 1999/2000 ዓ.ም የህዝብ ቆጠራ እንደሚያሳየን ከ85 ያላነሱ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ የግለሰብ ስብስቦች አሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ የየራሳቸው የመኖሪያ አካባቢዎች አሉአቸው፡፡ ከብዛት አንፃር ሲታይ ቁጥራቸው ከ19 ሚሊዮን በላይ የሆነ ሁለት ትላልቅ ብሔሮች፣ ማለትም አማራና ኦሮሞ ናቸው፡፡ በመሃከለኛ ደረጃ የሚታዩት ሲዳማ፣ ትግሬና ሶማሌ ናቸው፡፡ እና ጋሞ፣ አፋር፣ ሃዲያ፣ ወላይታና ጉራጌ በመሃከለኛ ደረጃ የሚታዩ ናቸው፡፡ ቁጥራቸውም ከ 1 እስከ 2 ሚሊዮን ይደርሳል፡፡ 18 ቱ ደግሞ

በየህዝባቸው ብዛት ከ1500 እስከ 8000 ይደርሳል፡፡ የቀሩት ሦስቱ በጣም ትንሾች ሲሆኑ ብዛታቸው፣ ቀዋማ 298፣ ሴ 320 እና ድሜ 891 ብቻ ናቸው፡፡

በቋንቋ ጥናት መሠረት እነዚህ የቋንቋ ስብስቦች የአፍሮ ኤዢያ ቋንቋ ቤተሰብ አባላት ሲሆኑ ሴማዊ፣ ኩሻዊ፣ ኦሞአዊና ናይሎ-ሰሐራዊ በሚባሉ ንዑስ የቋንቋ ቤተሰቦች ይከፈላሉ፡፡ የሕዝቦቹ ምንጭን በተመለከተ የአባይ /Nile/፣ የአዋሽ፣ የኦሞና የዋቤ ወንዞች ሸለቆዎችና አፋር ዲፕሬሽን አካባቢ መሆኑ አይቀምርː፡ ለምሳሌ ከአፈ ታሪክ አኳያ ኦሮሞዎች የተፈጠሩት በአዋሽ ወንዝ ዳርቻ እንዲሆነና ዋቃ ከሰማይ ወርዶ ከአዋሽ ወንዝ ጭቃ ወስዶ በሰው መልክ ጠፍጥፎ፣ ከዚያም ትንፋሹን ተንፍሶበት ወላቡን እንደፈጠረና፣ ወላቡም የኦሮሞዎች ቅድመ አባት/እናት ነው፡፡ ቢያንስ ቢያንስ 13 የሰው ዝርያዎችና ቅድመ አባት/እናቶቻችን ቅሪቶች በዚህ ዛሬ ኢትዮጵያ ብለን በምንጠራው አካባቢ እንደተገኙም አርኪዮሎጂስቶች ያስረዳሉ፡፡

ዛሬ የብሔር መብት ጥያቄን የሚያነሱትን የብሔር ፖለቲካ እንቅስቃሴዎች የሚቃወሙ የኢትዮጵያዊ ብሔርተኞች የሚያነሱት አንድ ነጥብ እኛ ሁላችን ተዋልደናል አንድ ነን የሚለው ነው፡፡ በእርግጥም የቋንቋዎቻችን ሥረ መሠረት አፍሮ አዚያዊ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አንዳንድ ቃለትና የቋንቋ አግባብ መዋቅር ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በሌላም በኩል ለራሳቸውም ሆነ ለቤት እንስሳት ምግብና ደህንነትን ለማፈላለግ የሰዎች ስብስቦች ካንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ የሌላ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑትን ስብስቦች ማግኘታቸውና ተጋብተው መቀላቀላቸው አይቀርም፡፡ የተፈጥሮ አደጋዎችና ጦርነቶች ሰፊ የሰዎች ፍልሰት ማስከተላቸው አይቀርም፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝቦች፣ ከነጭራሹ "አልተደበላለቁም፣ የቋንቋና የባሕል መወራረሶች አልነበሩም" ብሎ መካድ አይቻልም፡፡ ሆኖም ግን ምን ያህል ዘመናት መሆኑን ለመናገር ባይቻልም ለብዙ ጊዜ የየራሳቸው ማንነት ጠብቀው በየራሳቸው አካባቢ ሲኖሩ የነበሩ ሕዝቦች አሉ፡፡

ይህንን ሁኔታ በማየትም ነው አንዳንዶች ምሁራን ኢትዮጵያን "የሕዝቦች ሙዚየም ነች" የሚሉት፡፡ አዎን የብዙ እጽዋቶችና እንስሳዎች የሚገኙባት አገር እንድሆን ሁሉ የተለያዩ ቋንቋዎችና የባሕሎች ማህበረሰቦች አሉ፡፡

**3.2.2 የነበሩና አሁንም ያልጠፉ ባሕሎችና ልምዶች፡-** በኢትዮጵያ ባጠቃላይ ለማለት የሚቻል የግለሰቦችንና የስብስብ /group/ መብት የሚነኩ ባሕሎችና ልምዶች በመኖራቸውና አሁንም ከነጭራሹ እንዳልጠፉ

ይታወቃል፡፡ እነዚህን ባሕሎችና ልምዶች አንዳንዴም ካላጠናከሩ በስተቀር የሃይማኖትና የማህበረ-ኢኮኖሚና-ፖለቲካ ርዕዮተ ዓለሞች ሊያጠፉ አልቻሉም ዋና ዋናዎቹ ባሕሎችና ልምዶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. አባታዊነት /paternalism/
2. የወንድ በላይነት
3. የበኩር ልጅ ውርስ
4. የባሪያ ይዞታ
5. ካስት መሳይ ግንኙነት
6. ገዳይነት

አባት ወይም እሱ በሌለበት ጊዜ-ታላቅ ወይም ተከታይ ወንድሙ የሚስቱ /ሚስቶቹ/ እና የልጆቹ የበላይ ነው፡፡ ወሳኝ እሱ ነው፡፡ ሌሎቹ ትዕዛዙን ማክበር አለባቸው፡፡ ፈራጅና ቆራጭ እሱ ነው፡፡ ባጠቃላይ ንብረት ላይ የሚያዘው እሱ ነው፣ከንብረቱም የፈለገውን ይሸጣል፣ ይለውጣል፣ በስጦታ ያስተላልፋል፡፡ ወራሽ የበኩር ወንድ ልጅ ሆኖ /ባንዳንድ ቦታ የሴት የበኩር ልጁ ወራሽ ልትሆን ትችላለች፡፡ ወንድ በሴቶች ላይ የበላይነት አለው፡፡

በመማረክም ሆነ በግዢ ሰዎችን በባርነት መያዝ የተለመደ ነበር፡፡ ባንዳንድ አካባቢዎች ይህ ባሕል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሲሰራበት ነበር አንድ ሰው ወይም ከሱ የሚወለዱ ሰዎች ተገደው በሌላ አካል ለሥራ ጉልበታቸውን መስጠት ብቻ ሳይሆን የባለቤቱ ንብረት ስለሆኑ ይሸጣሉ በሕይወታቸው የመኖርና በአካላቸው ላይ የሚወስነው የባሪያው ባለቤት ነው፡፡ ባሪያዎች የራሳቸው ንብረት የላቸውም፡፡

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የሕብረተሰብ ክፍሎች በተጨማሪ ሌሎች የሰበአዊ መብቶቻቸው የሚጣሱ ስብስቦችም አሉ፡፡ እነዚህ ስብስቦች የተለያዩ የጉልበት ሥራ ያበረክታሉ፡፡ ሥራዎቹም ሽመና፣ ቀጥቃጭነት፣ ከብት ጥበቃ፣ የሸክላና የቆዳ ሥራ መሥራት ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህም ቢሆን የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው አይወስኑም በነፃነት የንብረት ባለቤቶች እንዳይሆኑ ይደረጋል፡፡ በአጠቃላይ ከሕብረተሰቡ ተለይተው እንዲኖሩ ይደረጋል፣ "ሸማኔ" ቀጥቃጭ ተበለው ይፀየፋሉ፡፡

የዚህ አይነት ስብስቦች በተለያዩ አካባቢዎች በተለያዩ ስሞች ይጠራሉ እንጂ የአያያዛቸው ባህሪ ተመሳሳይ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- በአማራ ፡- ወይጦ፣ በኦሮሞ - ዋተ ፣ በከፋና ቤንች፡- መንጃ፣ በወላይታ- አይሌ እና በሲዳማ - ሃዲቾ ተብለው የሚጠሩት የዚህ ዓይነት ስብስቦች ናቸው፡፡

በአካባቢአችን በአደን ትላልቅ አውሬዎችን የገደለ፣ ወይም በጦርነት ጠላትን የገደለ ሰው ከፍተኛ ክብር ይሰጠዋል፡፡ ገዳይ የገደለውን አውሬ ወይም ሰው ለሊት ይዞ ወደ መንደሩ ሲመለስ አጠቃላይ ሕብረተሰቡ የደመቀ አቀባበል ይደረግለታል፡፡ ሴቶች እሱን በዘፈን እያሞገሱ እንደሱ ጀግናና ገዳይ ያልሆኑትን የሰድባሉ ያፌዙባቸዋል፡፡ ገዳዩም ከሞተ በኋላ ሃውልት ይተከልለታል፡፡ በአወንታዊ ጎኑ ሲታይ ሕብረተሰቡን ከአደጋ መከላከልና አገርን ከጠላት መከላከል አስፈላጊ ስለሆነ ለጀግኖች ክብር መስጠትና ሐውልት ማኖር አስፈላጊ ነው፡፡ ሆኖም ግን በአሉታዊ ጎኑ ወንድነት፣ አሸናፊነት፣ ገዳይነት፣ ከመጠን በላይ ክብር ሲሰጠው በሰዎች ባህርይ ላይ ተፅእኖ አያሳድርም ለማለት አይቻልም፡፡ ፍፁም አሸናፊነትና ሰጥቶ በመቀበል ላይ ያልተመሠረተ ፣በመደራደር ላይ ያልተደረሰ ስምምነት፡ የመታረቅና የመቻቻል ፍላጎት ያለመኖር ከዚህ ዓይነት የወንድነትና የገዳይነት  አስተዳደግና ልምድ የመነጨ ይመስለኛል፡፡ የአክሱም ሃውልት፣ የኦሮሞ ከለቻ የወንድ ብልት ምስል፣ እንዲሁም አንዳንድ የባህል ዘፈኖችና ሰነ ስርዓቶችንም የማንነቶ ማስታወሻና ማስጠበቂያ ስልቶች ቢሆኑም፣ በባህሎቻችንና በልምዶቻችን ውስጥ የነበሩትንና ያሉትን የሰብአዊ መብቶች ረገጣ ሊያስረሱን አይገባም፡፡

### 3.2.3 የነበሩ ሥርዓቶች

ዛሬ ኢትዮጵያ ብለን በምንጠራው ግዛትና በአጎራባች አካባቢዎች የተለያዩ ማእከላት የነበራቸው ሥርዓቶች እንደነበሩ ታሪክ ይነግረናል፡፡ ሆኖም ግን ከአክሱም መንግስት (state) በፊት ስለነበረው ደአማት መንግስት ብዙም አናውቅም፡፡ ዛሬ ደብረ ዳሞ፣ ቡሬ ዳሞትና፣ ዳሞት ገሌ የሚባሉ የቦታ ስሞችና ደሞተ የሚባሉ ጎሳዎች የዳአማት መንግስት ቅሪቶች መሆን አለመሆናቸውን መናገር አይቻልም፡፡

አክሱምን ማዕከል ያደረገ፣ በክርስትና ሃይማኖት ተከታይ የሆነ የነገሥታት ዳይነስቲ ተፈጥሮ የግዛት መስፋፋት ሳይካሄድ  እንደነበረ እናውቃለን፡፡ የዚያ መንግሥት ስፋት እስከ የት ይደረስ እንደነበር ባናውቅም በደቡብ እስከ አሶሳ፣ በሰሜን እስከ ነቢያ በመስራቅ ቀይባህርና ሕንድ ውቅያኖስ ከዚያም እስከ የመን የደረሰ እንደነበር የታሪክ ፀሐፊዎች ግምት አለ፡፡ በአክሱም ግዛት ስር የነበሩትንና ዛሬም ማንነታቸውን ጠብቀው የቆዩ ህዝቦች እንደበሩ ጥቆማዎች አሉ፡፡ በዚያን ጊዜ በሰርዓቱ ስር የነበሩ ህዝቦችና ግለሰቦች ሁኔታ ምን ይመሰል እንደነበሩ አሁን ማውሳት ያስቸግራል፡፤ ሆኖም ግን ላይ የጠቀስኳቸው ባህሎችና ልምዶች ተግበራዊ እንደነበሩ መገመት ይቻላል፡፡ የአክሱም ነገሥታትም በአምላክ እንደተመረጡ የሚያምኑ (Devine) ፍጹማዊ (Absolute) ሞናርኮች ነበሩ፡፡

የአክሱም መንግስት፣ በቤጃ ጥቂቶች (ዮዲት- ከቤጃ መሪዎች አንድዋ ነበረች) ከተዳከመና ከወደቀ በኋላ ማዕከሉን ላሊበላና የአገውን ሕዝብ ማዕከል ያደረገ መንግስት ከ11ኛ እስከ 12 ኛ መቶ ዓመት ተነስቶ ነበር፡፡ የላሊበላ መንግስት ይከተለው የነበረው ርዕዮተ ዓለም ክርስትና ነበር፡፤ ግዛቱ ወደ ደቡብ መስፋፋቱን

የሚጠቁሙ ጭብጦችም አሉ። የአዋሽና የእንጦጦ ዋሻ ቤተክርስቲያኖች  የላሊበላን ጊዜ ባሕል ያስታውሰናል። በትግራይና በጉራጌ ዘፎኖች የሚሰማ "ላሎ" "ላሎዬ" የሚባል ቃልና በማዕከልና በምዕራብ ኦሮሚያ ተሰራጭተው የሚገኙ ላሎ ጎሳዎችም ከላሊበላ መንግስት ጋር ግንኙነት ነበራቸው ወይ የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም።

በዚህም ከአዲስ አበባ በስተደቡብ እስከ ዝቋላ ድረስ በምዕራብ፣ በመስራቅና በሰሜን ሸዋ አካባቢም ላሎ የሚባል መንግስት እንደነበረ ታሪክ ይነግረናል። በአማራው ሰሜን ሸዋ ዞን ውስጥ ላሎ ምድር የሚባል ቦታም አለ የላሊበላ መንግስት ወደነዚህ አካባቢዎች ግዛቱን እያስፋፋ በነበረበት ጊዜ  በአዋሽ ወንዝ አካባቢ ሰራዊቱን ገጥሞ አሸንፎ ነበር ተብሎ የሚነገርለት ሕዝብ አንዱ የወርጂ (ወርዳይ ወረዳኢ) ኦሮሞ ነው። የላሊበላ ነገሥታትም ፍጹማዊ መለኮታዊ (Devine) ገዢዎች እንደነበሩ ይገመታል።

የላሊበላ መንግሥት በሰሜን ተቋቁሞ ወደ ደቡብ በመስፋፋት ላይ በነበረ ጊዜ ባዛሬው መሃል በከፊል የዛሬ ደቡብ ኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍልና ፣ በምስራቅ ተቋቁመው በየአቀወጣጫው መስፋፋት ጀምረው የነበሩ የሙዝሊም ሱልጣኔቶችም ነበሩ።፤ እነዚህም ይፋት፣ አዳል፣ ደዋሮ፣ ሃዲያ፣ ሸርካ፣ ባሊና ደራ ይባሉ ነበር። እነዚህ ሱልጣኔቶች ከእነአጼ አምደፅዮን፣ አጼ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን አብዛኞቹ ልእልናቸውን ሲያጡ፣ አንዳንዶቹ እስከ 16ኛው መቶ ክፍለዘመን ራስን እየተከላከሉ ዘልቀው ነበር የአዳል ስልጣኔት  ማዕከሉን ከአፋር (አውሳ) ወደ ሐረር በማዛወር እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን  ነፃነቱን ጠብቆ ቆይቷል።

በሌላም በኩል ደግሞ ከ13ኛ መቶ ክፍለ ዘመን እስከ 16ኛመቶ ክፍለ ዘመን የነበረውና ሰለሞናዊ የምንለው የሸዋ መንግስት ነበር። በቀጣይነትም ባይሆን የሸዋው መንግስት ግዛት በምእራብ እስከ ቱለ ወለል (ቁሌም)፣ በደቡብ እስከ ከፋ ወላይታና ገሙጎፋ፣ በምስራቅ እስከ ህንድ ውቂያኖስና ቀይ ባህር ደርሶ ነበር ይባላል።

በ16ኛው መቶኛ ክፍለ ዘመን አካባቢ የሸዋው ክርስቲያናዊ ሰሎሞናዊ ዳይናስቲ በእስላሙና በአዳሉ መሪ በሱልጣን ግራኝ መሃመድ ተሸነፈ። ግራኝ መሀመድም አብዛኛውን የዛሬ ኢትዮጵያ ግዛት ከደቡብ እስከ ትግራይ፣ ጎንደር/ጎጃም ከምዕራብ ኦሮሚያ እስከ አፋር ሶማሊ ከቁጥጥሩ ሥር አስገብቶ ለ14 ዓምት አስተዳድሮአል።፤ ግራኝ መሃመድ ከሞተ በኂላ የእስላም ሱልጣንት ግዛት በአፋር በሐረርና እንዲሁም በምስራቃዊ ድንበሮች ምናልባትም እስከ ሃርጌሳ ድረስ ይደርስ ነበር።

ከአስራ ስድሰተኛው መቶኛ ክፍለ ዘመን በኂላ ሌላ ሂደት መከሰት ጀመረ በሸዋና በሙዝሊሙ ሱልጣኔቶች ዘመን ክርስቲያንም እስላምም ያልሆኑ ኦርምኛ ተናጋሪ የነበሩ ማኅበረሰቦች በዛሬይቱ ደቡብ ምስራቅ፣ ደቡብ እንዲሁም እስከ ሸዋና ወሎ በግብርናና በከብት እርባታ ላይ ተመስርተው ይኖሩ ነበር።

እነዚህ የኦሮሞ ማህበረሰቦች በያሉበት አካባቢ በገዳ ስርዓት ላይ የተመሠረተ አስተዳደር መስርተው ሲኖሩ የነበረ ቢሆንም ማእከሉን ኦዳ ነቤ (ዱከም) አካባቢ የነበረ የገዳ ኮንፌድራላዊ አገዛዝ (state) በአጼ አምደ ጽዮን

ጊዜ እንደነበረ ታሪክ ይጠቁማል፡፡ ሆኖም ግን በሰሜን ክርስቲያናዊ ነገሥታት በሌላም በኩል ከምሥራቅ የሙዝሊም ሱልጣኔቶች ሲያደርሱበት በነበረው ጥቃትና ተፅዕኖ ምክንያት የኦሮሞ ኮንፌድራሉ ማዕከል ወደ ባሌው ወላቡ ተዘዋውሮ ነበር በጊዜ ሂደት ኮንፌደራሲው እንደ አዲስ በመደራጀት በ16ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ምዕራብ.፣ ወደ ሰሜንና ወደ ምስራቅ በማጥቃት የዛሬውን ኦሮሚያ አብዛኛውን አካባቢ መልሶ ከቁጥጥሩ ስር በማስገባት ከዚያም ባሻገር በምዕራብ፣ በሰሜንና በምስራቅ በሌሎች ስርአቶች ስር የነበሩት አካባቢዎች ለመያዝ ችሎአል፡፡ ከዚያም በኂላ እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ክርስቲያናዊ የድሮ ኢትዮጵያ መንግስት ግዛት በደቡብ የዛሬውን የአማራ ሰሜን ሸዋን፣ በምዕራብ ጎጃምን፣ በሰሜን ወሎ፣ ላስታ፣ የጁ፣ ራያ ሰሜንና ትግራይን እና ባሕረ ነጋሽ ብቻ ያጠቃል ነበር፡፡ በሌላ በኩል ከኦሮሞዎች ግዛት በስተደቡብና በስተምዕራብ ደግሞ ባንድ በኩል ከገዳ ስርዓት ጋር ተቀራራቢነት ባላቸው የኩሻዊ ቋንቋ ቤተሰብ አባላት የራሳቸው አካባቢ ይዘው የቋንቋና የባህል ማንነትና የአስተዳደር ስርዓት ይዘው ቀጥለው ነበር፡፡ እነዚህ ህዝቦች ባንድ በኩል ከበስተምስራቅና በስተሰሜን ከኦሮሞዎች ሲደርስባቸው የነበረውን ከበስተምእራብ ደግሞ ከወላይታ ነገስታት ሉአላዊነታቸውን ጠብቀው እስከ 19ኛው መቶኛ ዓመት ለመኖር ችለዋል፡፤

በተጨማሪም በዛሬው የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ጥንታዊ የወላይታ፣ የከፋና የቦንጋ መንግስት ነበሩ፡፡ እነዚህ ነገስታት ክርስታናዊም ሆነ እስላማዊ ርዕዮተ ዓለም ተከታዮች አልበሩም፡፤ ስልጣናቸውን ከፈጣሪያቸው የተቀበሉ ብለው የሚያምኑ ፍጹማዊ ነገሥታት ነበሩ፡፡

እነዚህ መንግስታት የኦሞ ወንዝ ምስራቃዊና ምእራባዊ እንዲሁም በጎጀብ ወንዝ ሰሜናዊና ደቡባዊ እንዲሁም በባሮ ወንዝ ደቡባዊ አካባቢዎች በሚገኙ ደጋማ አካባቢዎች በግዛትነት ይዘው ነበሩ፡፡

በነዚህ ግዛቶች በስተደቡብ እና ምእራብ ይኖሩ የነበሩ ህዝቦች በቆላማ አካባቢዎች በከብት እርባታና በግብርና ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ ይዘው በዘላልነት ካንድ ቦታ ወደ ሌላ እየተንከራተቱ ይኖሩ ነበር፡፡

በየጊዜውም ከደጋማ አካባቢ በሚመጡ አዳኞች የዘረፉና የባሪያ ፈንጋይ ሰለባዎች ሆነው ኖረዋል፡፡ ሆኖም ግን የራሳቸው መከላካያና መተዳደሪያ ስለነበራቸው የራሳቸውን ማንነት በመጠበቅ ለዘመናት ኑረዋል፡፡

### 3.2.4 የዛሬይቱ (ወይም ዘመናዊ) ኢትዮጵያ አመሠራረትና አጠባበቅ

#### 3.2.4.1 <u>ከአፄ ሚኒሊክ እስከ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመን መጨረሻ</u>

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ከ16ኛው እስከ 19ኛው መቶኛ ዓመት ድረስ ኢትዮጵያ (በሌሎች አቢሲኒያ) ተብላ የምትታወቀው አገር ግዛትም ባሕረ ነጋሽ፣ ትግራይ፣ ሰምን፣ ቤገምድር፣ ጎጃም፣ ራያ፣ የጁ፣ ላስታ . ወሎና ሸዋ (የዛሬው የአማራ ክልል ሸዋ ዞን) ብቻ የሚያጠቃልል ነበር፡፤

ማዕከሉን ጎንደር ያደረገ አስተዳደር ቢኖርም አስተዳደሩ ማእከላዊ አልነበረም፡፡ የተለያዩ መሳፍንት የየራሳቸውን ግዛት ይዘው በጎንደር የበላይነት ይዘው ሌላውን አካባቢ ከቁጥጥራቸው ስር ለማስገባት ይፎካከሩ ነበር፡፡ ያቺን ኢትዮጵያ በአንድ ማዕከላዊና ዘመናዊ አስተዳደር መዳፍ ስር ለማስገባት ራዕይ የነበረውና እንቅስቃሴ ያደረገው መሪ በ1986 የሞተው አፄ ቴዎድሮስ ነበር፡፡ የአፄ ቴዎድሮስ ህልም የድሮዋን ኢትዮጵያ ባንድ ማዕከላዊ አስተዳደር ስር ማስገባት ብቻ ሳይሆን በዚያን ጊዜ አባባል ጋላወንና እስላሞችን በማጥፋት እስከ እየሩሳሌም ድረስ የኢትዮጵያን ግዛት ማስፋፋት ነበር፡፡ ሲያደርግ በነበረው እንቅስቃሴም ከፍተኛ ጭካኔ የሞላበት ድርጊቶችን ፈጽሞአል፡፤ ሆኖም ግን ህልሙ ሳይሳካለት ቀረ፡፡

አጼ ቴዎድሮስ ከሞተ በኋላ ላጭር ጊዜ ነግሦ የነበረው አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ነበር፡፤ የአጼ ተክለጊዮርጊስ ተቀናቃኝ የነበረውና ከእንግሊዞች የጦር መሣሪያ ድጋፍ ያገኘው የትግሬው ካሣ ተክለጊዮርጊስን አሸንፎ ንጉሠ ነገሥት አጼ ዮሐንስ ሆነ፡፡ አፄ ዮሐንስ ማዕከሉን መቀሌ ቢያደርግም አብዛኛውን የድሮዋን ኢትዮጵያ በአንድ ማዕከላዊ አስተዳደር ስር ለማስገባት ችሎአል፡፡ ከሸዋው ሚኒሊክ ጋር በመተባበር አፈንግጠው የነበሩትን ራያ፣ የጁንና ወሎን የጨከነ እርምጃ በመውሰድ አስገበሩአቸው፡፡ ሆኖም ግን የአጼ ዮሐንስ አስተዳደር ፍጹም የተማከለ ሳይሆን ፌደረላዊ መልክ የነበረው ነው፡፡ የአካባቢውን መሪዎች የራስና የንጉሥ ማዕረጎች እየሰጠ አካባቢውን እያስተዳደሩትና በየጊዜው የሚፈልባቸውን ግብርና አገልግሎት እንዲሰጡት አደረጉ፡፡ የግዛቱን አንድነትንም በርዕዮተ ዓለም አንድ ለማድረግ ሰባት አቡኖችን ከግብፅ በማምጣት በየአካባቢው ሾመው እነ ራስ ዓሊንም ንጉሥ ሚካኤል በማለት ክርስትና አስነሰአቸው፡፡

በሌላም በኩል ግዛታቸው እንዲያስፋፋቸው  የሸዋውን ንጉስ ሚኒሊክን ወደ ደቡብና ወደ ምሥራቅ እንዲዘምቱለት የጎጃሙን ንጉስ ተክልሃይማኖትን ደግሞ ከአባይ ወንዝ በስተደቡብና ከግቤ/ኦሞ ወንዞች በስተምዕራብ ያሉትን አካባቢዎች እንዲወሩላቸው አዘዙ፡፡

በዚህ ዓላማ ማስፈጸም ሂደት ላይ እያለ ነበር አፄ ዮሐንስ በመተማ በደርቡሾች የተገደሉት፡፡

በዚህ ዘመን በተጓዳኝ ሌላም ክስተት ነበር፡፡ ዘመኑ በአውሮፓ የእንዱስትሪ ካፒታሊዝም እድገት በከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ደንበርን ጥሶ ወደ ሌሎ ዓለም ክፍሎች የሚስፋፋበት ጊዜ ነበር፡፡ በመሆኑም ካፒታላዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶች ያደጉባቸው አገሮች ለሥርኣቱ አስፈላጊ የሆኑትን የዓለም ክፍሎች በኮሎኒ ለመያዝ መሽቀዳደም ጀምረው ነበር፡፡ በዚህም ሂደት እንግሊዞች በግብፅ ተልዕኮነት ሱዳን፣ ኤርትራንና ሐረርን ያዘች፡፡ በኋላም እንግሊዝ ግብጽን፣ ሱዳንን ኬንያንና ሰሜናዊውን ሱማሌን (ሃርጌሳን) ያዘች፡፡ የእንግሊዝ ተቀናቃኝ የነበረችው ፈረንሳይ ደግሞ ጂቡቲን ያዘች፡፡ ተቀናቃኟዋ ፈረንሳይን ከአካባቢው ለማግለልም አርትራንና ደቡብ ሱማሊያን እንድትይዝ እንግሊዝ ኢጣሊያንን ገፋፋች፡፡ ስለሆነም አጼ ሚኒሊክ ይህን ሂደት ይከታተሉ ስለነበር ይህ የአውሮፓውያን ተሰፋፊነት ደስ አላላቸውም በመሆኑም አውሮፓዊያኑ አካባቢውን እንደቅርጫ

ሳይከፋፈሉ በአጣዳፊነት እርምጃ መውሰድ ነበረባቸው። አጼ ዮሀንስ የሰጡአቸውን ተልዕኮ ከግቡ ለማድረስም ሆነ አውሮፓውያኑን ለመጋፈጥ የመሣሪያ ሃይል ያስፈልጋቸው ነበር። መሣሪያን ለመግዛት ደግሞ በአውሮፓ የሚፈልጉትን ምርቶች ማቅረብ አስፈላጊ ነው። ምርቶቹ የሚገኙት ደግሞ ከ19ኛው መቶኛ ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ግዛት ስር ያልነበሩ፣ ከአባይ እና ከሸዋ በስተደቡብ የሚገኙ ነፃና ሉአላዊ አካባቢዎች ነበሩ። ስለሆነም አጼ ሚኒሊክ በተቻላቸው ፍጥነትና መጠን እነዚህን አካባቢዎች መውረር ነበረባቸው። በዚህም ወረራ የዘመኑን የጦር መሣሪያዎች በመጠቀም ብቻ ሳይሆን በተላያዩ ሙያዎች (ጦርነትን ጨምሮ) እውቅና የነበረባቸውን አውሮፓውያን እንዲያገለግሉአቸው አድርገዋል።

አውሮፓውያን በአካባቢው አንዳይጫረቱአቸው የማድረግ ፍላጎታቸውን በግልጽ የሚያስቀምጥ ለንግሥት ቪክቶሪያ በ1883 ከጻፉት ደብዳቤ ሌላ የታሪክ መረጃ ሰነድ አያስፈልግም። በዚህ የወረራ አንቅስቃሴ በአጼ ሚኒሊክ ግዛት ስር የገቡ አካባቢዎች የሚከተሉት ናቸው።

- 1865 የቱለመና የወሎ ኦሮሞ
- 1871 ቀሪው ወሎና መጫ ኦሮሞ
- 1873 ሌቃ፣ አርሲ፣ ኢቱና የግቤ ኦሮሞ
- 1880 ሐረርና አፋርን ቀሎ ቀሪው ሌቃ ኦሮሞ እና ጉራጌ

  ንጉሠ ነግስት ሆነው በሸዋ ጎጃም፣ ቤጌምድር፣ ትግራይና ሎሎችም አካባቢዎች ያጠቃልላል።
- 1886 ወላይታና ሲዳማ
- 1890 አኙአክ፣ ቤንች. ኦጋዴን፣ ኮንሶ. ቡርጂ፣ አሉ-ኦርሞ፣ ባሌ-ኦሮሞ
- 1903 ማጂ ፣ ቦረና ኦርሞና አፋር

  በወረራው ወቅትና ከዚያም በኋላ የደረሰውን የሰው ህይወት መጥፋት የንብረት መውደም የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በተመለከተ አሁን ለመዘርዘር ጊዜ አይኖረን።

ከዚህ በመቀጠል የሚነሳው ጉዳይ የአጼ ሚኒሊክ የግዛት መስፋፋት ምን አይነት ማህበረ ኢኮኖሚያዊና ፓለቲካዊ ይዘት የነበረው የሚለው ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ አጼ ሚኒሊክ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ በኋላ በቀድሞው ኢትዮጵያ ላይ የበላይነት ሲቀዳጁ በየአካባቢው የነበሩትን ገዢ መደቦች አልነኩም። ቢሆንም በርሳቸው ዙሪያ የነበሩ መኳንንት ባብዛኛው የሸዋ አማራ ተወላጆች ነበሩ ለማለት ይቻላል።

አካባቢያዊ (Regional) ግንኙነት አንፃር የሸዋ በላይነት የነገሠበት ነበር ማለት እንችላለን። ሆኖም ግን በሰሜን ሸዋ በወሎና ትግራይ በአገው አካባቢዎች የአማርኛ ቋንቋ የበላይነት ቦታ እንዲይዝ ተደርጎአል። ከኢኮኖሚ አንፃር ድሮም የነበረው ፊውዳላዊ ስርዓት አንዲስፋፋ ተደርጎአል።

ከ1985 (እ.ኤ.አ) ዓ.ም በኋላ የተያዙት አካባቢዎች ሁኔታ ከዚህ የተለየ ነበር፡፡ አፄ ሚኒሊክ በ1883 በፃፉት ደብዳቤ እየወረሩ ያሉት አካባቢ ጥንት የኢትዮጵያ ግዛት አካል የነበሩ መሆናቸውን እንደሚያምኑ ይጠቁማል፡፡ አንዳንድ ምሁራንም ይህን እየደገፉ አፄ ሚኒሊክ የተበታተነች ኢትዮጵያን መልሰው አንድ አደረጉአት ብለው ይከራከራሉ፡፡ የግዛታቸው ስፋት የት ደርሶ እንደነበር በትክክለኛነት ለማወቅ ባንችልም አርግጥም በአጼ ሚኒሊክ የተያዘ አካባቢ አብዛኞቹ በአክሱም፣ በላሊበላና በሸዋ የክርስቲያን መንግስታት ይዞታና ጥላ ስር የነበሩ እንደነበር ታሪክ ይጠቁማል፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ አካባቢዎች ከ16ኛ መቶኛ ዓመት እስከ 19ኛው መቶኛ አመት ድረስ በኢትዮጵያ (በአቢሲኒያ) ግዛት ሥር አልነበረም፡፡ ሉአላዊነት ነፃነት የነበራቸው አካባቢዎች ነበሩ፡፡ ስለሆነም የአፄ ሚኒሊክና የደጋፊዎቻቸው መከራከሪያ ነጥብ አያዋጣም፡፡

አዲስ የተወረሩ አካባቢዎች ልዕልናና ነፃነታቸው ተገርሥሶ፣የነበራቸው የራሳቸው አስተዳደርና ስርዓት ፈርሶ በቦታው ሌላ ስርዓት እንዲተካ ተደርጎአል፡፡ በነዚህ አካባቢዎች ላይም ከማዕከል የተላኩ አስተዳዳሪዎች (ገዢዎች) ተሹመባቸዋል፡፡ አዲሱ ገዢዎች ቋንቋቸው፣ሃይማኖታቸውና ባህላቸው ከየአካባቢው ቋንቋ ሃይማኖትና ባህል የተለየ ነበር፡፡ እንዲያውም የየአካባቢው ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ባህልና ታሪክ ለማጥፋት ተንቀሳቅሰዋል፡፡

ከኢኮኖሚ አንፃር በአዲሶቹ አካባቢዎች ላይ የተዘረጋው ስርዓት በድሮይቱ ኢትዮጵያ የተለመደ ፊውዳላዊ ስርዓት አልነበረም፡፡ የተወረሩ አካባቢዎች በመልከኛና በጪሰኛ ስርዓት መሠረት እንዲበዘበዙ ነው የተደረገው፡፡ ገባሮችና ጪሰኞች በየጊዜው በዓይነትና በገንዘብ ከሚከፍሉት ግብር በተጨማሪ ለገዢዎቻቸውና (መልከኛ /ገዢ) አካባቢዎቹን ለመጠበቅ ለተሰማሩ ታጣቂዎች (ነፍጠኞች) በግዳጅ ነፃ የጉልበት ሥራ እንዲያከናውኑ ይደረግ ነበር፡፡ ታዲያ ይህ አሰራር በቀድሞይቱ ኢትዮጵያ ተንሰራፍቶ በነበረው ፊውዳሊዝም ጋር ምኑ ነው የሚመሳሰለው? አንዳንድ የጭቁን ህዝቦች መብት ጥያቄን የሚያነሱት ሁኔታውን የቅኝ አገዛዝ ስርዓት ነበር ይሉታል፡፡ ቅኝ አገዛዝ የሚለውን የአማርኛ አገላለጽ ከእንግሊዝኛው ኮሎኒያሊዝም ጋር የሚያመሳስሉም አሉ፡፡ በኔ አረዳድ የዚህ አይነት የማህበረ ኢኮኖሚ ባህላዊና ፖለቲካ ሥርዓት በሰሜን በላቲን አሜሪካ፣ በደቡባዊ አፍሪካና በፓለስቲና የተያው ሰፋሪ (setler) ኮሎኖሊያሊዝም ጋር ይመሳሰላል፡፡ እንጂ በ19ኛው መቶኛ ዓመት መጨረሻ ላይ የታየው የአውሮፓ ኢምፔሪያሊዝም የኮሎኒያሊዝም መስፋፋት አይነት አይደለም ስለሆነም በኢትዮጵያ የታየው ወረራና ይዞታ ሉዓላዊ የነበሩትን አካባቢዎች በመሳሪያ ሃይል አስገድዶ በባዕድ በኢኮኖሚያዊ ባህላዊና ፖለቲካ ብዝበዛና ጭቆና ነበር እንጂ ለኮፒታሊስታዊ ሥርዓት መገዛት አልነበረም፡፡

ያም ሆነ ይህ በአጼ ሚኒሊክ በራሳቸው አገላለጽ የተከሰተው ሂደት <u>ማቅናት</u> ነበር፡፡ ቅኝ ግዛትም ከዚህ የአማርኛ ቃል የመጣ ይመስለኛል፡፡ ይህ አፄ ሚኒሊክ የተጠቀሙበት ቃል ለብሔር ጥያቄ የምንሰጠው መልስም ተገቢ የሆነ አቅጣጫ የሚጠቁመን ይመስለኛል፡፡

ከአፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግስት በኋላም እሳቸው የተከሉት ስርዓት እስከ አፄ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት መጨረሻ ድረስ ቀጥሎበት ነበር፡፤ በአፄ ኃይለስላሴ ዘመነ የተቀየረ ነገር ቢኖር የጭቆናንና የብዝብዛን ሥርዓት በዘመናዊ፣ ቢሮክራሳዊ፣ በዘመናዊ ፖሊስና ሠራዊት ማዳበር ካልሆነ በስተቀር የተሻለ ሁኔታ አልተፈጠረም እርግጥ ጥገኛ ካፒታሊዝም መቆጥቆጥ ጀምሮ ነበር፡፡ ሥልጣን በንጉሡ እጅ ተከማችቶ ንጉሡ በሁሉም ጉዳዮች ፈላጭና ቆራጭ ነበሩ፡፡ ይህንንም ስልጣን በሰለሞንና ሳባ በኩል ከፈጣሪ የተሰጣቸው ሆኖ ያዩት ነበር፡፡ በ1931 ዓ.ም (እኤአ) የታወጀው ሕገ መንግስት አገሪቱ የመንግስታቸው ንብረት እንደሆነች፣ አገርና ሕግ በንጉሡ እንደተወሃዱ፣ ዙፋን በሳቸውና በልጆቻቸው ብቻ መያዝ እንዳለበት፣ አማርኛ ቋንቋ ብቻ የመንግስት እውቅና እንዳለውና በሱ ብቻ መሠራት እንዳለበት፣ በኢትዮጵያ ዙፋን የሚቀመጥ ሰው  የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ መሆን እንዳለበት፣ ባጠቃላይ ንጉሡ ገደብ የሌለው ስልጣን እንደነበራቸውና እሳቸው በሕግ በላይ ሆነው በአገሪቱና በሕዝቡ እንዲሁም በአገሪቱ መንፈሳዊና ሲቪል ጉዳዮች ላይ እሳቸው ብቻ የሚወስኑ መሆኑን ይዘረዝራል፡፡

አገራችን በኢጣሊያ በተወረራች ጊዜ አገሪቱ ለአምስት አመታት በኮሎኒነት ተይዛ እንደነበርና የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በሰፊው ሲካሄድ የነበሩ መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ስለሆነ እዚህ መዘርዘር አያስፈልግም ፡፡

በ1955 ዓ.ም (እ.አ.አ) የተሻሻለው ሕገ መንግስትም ቢሆን 28 አንቀጾች ስለሰብአዊ መብቶች አከባበር ቢያወሱም በተጨባጭ ሁኔታ ግን የተለወጠ ነገር አልነበረም፡፡ በተለይም በአንቀጽ 16 ላይ “ንጉሥ አይከሰሰም፣ አይገሰጽም “ ብሎ ንግሡን ከሕግ በላይ ያስቀመጠው ድንጋጌ የነበረው ልምድ እንዲቀጥልበት አድርጎአል፡፡

የነበረው ሰብዓዊ መብቶች ጥሰት (የብሔርና የግለሰብ) ከብደት አፍንጫው ላይ የደረሰ ሕዝብ አምቢ ብሎ መነሳቱ አይቀሬ ስለነበር በየአካባቢው የተለያዩ መነሳሳቶች (Revolt) ይከተሰቱ ነበር፡፡ እነዚህን መነሳሳቶች ለማፈንም ጭካኔ የተሞላባቸው የቅጣት እርምጃዎች በየአካባቢው ይወስዱ ነበር፡፡ ከነዚህም ውስጥ በራያ፣ በኤርትራ፣ በጎጃም፣ በባሌ፣ እዚህ አዲስ አበባ በመጫ ቱለማ ማህበር አመራርና በዩኒቨርሲቲ እንዲሁም በአኙዋኮች ላይ የተወሰዱት እርምጃዎች ዋና ዋናዎቹ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ መንደሮች በቦምብ ጋይተዋል ንፁሐን ልጆች፣ እናቶችና ሽማግሌዎች ተጨፍጭፈዋል፡፡ ብዙ

ሰዎች ታስረዋል ቶርች ተደርገዋል፤ ተገድለዋል። መሠረታዊ የዜጎች ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች አይከበሩም ነበር።

### 3.2.4.2 - የንጉሠ ነገሥት መንግስት ባሕርይ በብሔርና ከግለሰብ መብት አኳያ

እንደሚታወቀው፣ የአንድ አገር ሕገ መንግሥት፣ ሕጎችና ደንቦች መመሪያዎችን የሚወጡት ገዢው ክፍል በያዘው መርህ ላይ የተመሠረተ ነው። ውሳኔዎችም የሚሠጡት በመርሁ መንፈስ ይሆናል። አደረጃጀቶች እና የፈፃሚ አካላት አመዳደብም የመርሁን ተግባራዊነት የሚደግፉ መሆን አለባቸው። አፈጻጸሞችና እንቅስቃሴዎች የሚመዘኑት ከመርሆቹ ጋር የተስማሙ ነበሩ ወይስ አይደሉም የሚሉትን ጥያቄዎች ከግንዛቤ መውሰድ አለባቸው።

በአጼ ሚኒሊክ የተመሰረተችው ኢትዮጵያና ከሳቸው ዘመነ መንግስት እስከ አፄ ሃይለስላሴ ዘመነ መንግስት መጨረሻ የነበሩት መንግስታት አመለካከታቸውና እይታቸው፣ ያወጡ የነበሩት ሕጎችና እንቅስቃሴዎች በምን መርሆዎች ላይ እንደተመሰረቱ ካልተረዳን በዘመናቱ የነበረውን የብሔርና የግለሰብ መብት ጥያቄ አያያዝ ወይም አመላለስ በተገቢው መንገድ ግልጽ አይሆንም። ስለሆም በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት አዋጅ ውስጥ የተዘረዘሩትን የብሔርና የግለሰብ መብቶችን ነገሥታቶች ሲከተሉአቸው ከነበረው መርሆዎችና ውጤት ጋር ለማነፃፀር እንዲያመች ከዚህ በመቀጠል መርሆዎቹን በዝርዝር እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

1. ንጉሡ ከሁሉም በላይ የሆነ ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤት ነው።
2. የንጉሡ ሥልጣን ምንጭ አምላክና ከሰለሞንና ከሳባ ዘር የተወለደ በመሆኑ ነው።
3. ንጉሡ ከሁሉም የላቀ ኃይል ነው። (power)
4. ንጉሥ አይከሰስም፣ አይነቀፍም። ማንም ክስ አያቀርብበትም (የ1955 ዓ.ም(እ.ኤ.አ) አንቀጽ 16
5. ሥልጣን ሁሉ በንጉሡ እጅ የተከማቸ ነው የጠቅላላው የአገሪቱ መሬትና ሕዝብ የንጉሥ ተገዥ ነው። በአገር፣ በሕዝብ፣ በመንፈሳዊና ሲቪል ጉዳዮች የሚያዘው ንጉሡ ነው። ሰው መኖር ወይም ያለመኖር ላይ የሚወስነው እሱ ነው፤ የሚሾምና የሚሽር፣ የሚቀጣና የሚምር ንጉሡ ነው። በጦርነትና በሰላም ጉዳይ የሚወስንና ከፈለገው ጋር ግንኙነት የሚፈጥር እሱ ነው።
6. የአገሪቱ አወቃቀር ገንጉሡ ስልጣን ሥር የተማከለ መሆን አለበት።
7. ንግሥና ከንጉሡ ቤተሰብ መውጣት የለበትም ወራሽ ንጉሥ በአባቱና በጦር መኳንንቱ ይሾማል። ወራሹ የሚመረጠውም ከንጉሡ ወንድ ልጆች ወይም ከንጉሡ ወንድሞች መሃከል መሆን አለበት።
8. ንጉሡ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይና ጠባቂ ነው።ሃይማኖቱን ወደ ሌላ መቀየር የለበትም።
9. የአገሩ ቋንቋ የንጉሡ ቋንቋ መሆን አለበት። አማርኛ

10.ንጉሡ ስልጣኑን ተግባራዊ የሚያደርገው በሃይል (ጉልበት) በማስገደድ ነው

11. ንጉሱ በፈለገው መጠን፣ በፈለገው ቦታና ዓይነት ንብረት ሊያፈራ ይችላል፡፡

12. ያገሩ ዜጎች (ተገዥዎች) ንጉሡ ወይም የንጉሡ መንግሥት የሚያስቀምጠውን ግዳጅ መፈጸም ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ ግዳጆችም የንጉሡ መንግስት የመያውጃቸውን ሕጎችና፣ ደንቦች፤መመሪያዎች ማክበር ፣ ግብር መክፈልና የጉልበት አገልግሎት መስጠት (ውትድርናን ጨምሮ)፣ በምርጫ ላይ መሳተፍ የሚሉ ናቸው፡፡

13. የንጉሡ ተልእኮዎች (mission) " የጋሎችንና የእስላሞች አጥፊ" አቅኚ የአገርና ያገር ሕጎች ጠባቂ፣ የአገር አንድነት ጠባቂ እና የአፍሪቃ መሪ የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

ይህም ሆኖ በ1931(እ.ኤ.አ) የአገሪቱን መንግስትና አስተዳደር መልክ ለማስያዝና ዘመናዊ ለማድረግ ተብሎ ንጉሡ " ለሚወዱት ሕዝብ " ሕገ መንግሥት ሠጥተዋል፡፡ በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ መብቶች ናቸው ተብለው የተቀመጡት

ሀ. ወደ ንጉሡ አቤት ማለትና ይግባኝ ማለት

ለ. Privacy

ሐ. የቤተሰብ ንብረት የጋራ መሆን

መ. የግል ንብረት መያዝ

ሠ. የፍቺ መብት ይገኙበታል፡፡

የ1952 (እ.ኤ.አ) የኤርትራ ሕገ መንግሥት በተባበሩት መንግስታት ከታወጀ በኋላ የኢትዮጵያም ህገመንግስት ከኤርትራው ጋር ለማጣጣም ስለተፈለገና ከውጭም ከውስጥም ግፊቶች ስለነበሩ የ1931(እ.ኤ.አ) ማሻሻል ስለተፈለገ የ1955 (እ.ኤ.አ) የተሻሻለው ሕገ መንግስትን ንጉሡ ለሚወደው ሕዝባቸው ሰጥተዋል፡፡ የሚገርመው የሕገ-መንግሥቱ 28 አንቀፆች የሰብአዊ መብቶችና መሠረታዊ የዜጎች መብቶችና የፖለቲካ መብቶች የሚያስከብሩ ናቸው፡፡ ታዲያ ምን ያደርጋል የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ይመራበት የነበረው መርሆዎች እላይ የተዘረዘሩት ስለሆኑ ተግባራዊ አፈጻጸሙ የተቃራነው ነበር ማለት ይቻላል፡፡

### 3.2.4.3 ጭቆና አፈናና ውጤት

መጠኑ አሁንም በትክክል ባይገመትም በሚኒሊክ ወረራ ጊዜ በተወረሩ አካባቢዎች ከፍተኛ መጠን ያለው ንብረት ወድሞአል በመቶ ሺ የሚቆጠር የሰው ሕይወት ጠፍቶአል፡፡ ሺዎች አካለ ጎደሎ ሆነዋል፡፡ ተማርከውም በባርነት ተይዘዋል ተሸጠዋል፡፡

በየአካባቢው የነበሩ መሪዎ ብዙዎች ሲገደሉ ብዙዎች ወደ ደብረብርሃን እንዲመጡ ተደርገው ታስረዋል፡፡ ብዙዎችም በእስር ቤት ነው የሞቱት እንደምሳሌ እና የወላይታው ንጉስ ጦና፣ የከፋው ንጉሥ ጋኪ ሻሮቺ እና የቄሎሞ ወለጋው ንጉሥ ጆቴ ቱሉን መጥቀስ ይቻላል፡፡ አንዳንድ ነባር የየአካባቢ መሪዎች በፈቃዳቸው እጅ ሰጥተው በበታቸ ሹማምንትነት እዚያ ሲሾሙ የተቀሩት ግን ከማእከል በተላኩ ሹማምንት መገዛት ጀመሩ፡፡ በየአካባቢውም ሆነ በማዕከል ተሿሚ ለመሆን ክርስተያን መሆን የግዴታ ነበር፡፡ የአካባቢው ሕዝብ በመገደድ በገፍ ክርስትና እንዲነሳ ተደርጎ የክርስቲያን ስም እንዲቀበል ተደረገ፡፡

በሃገሪቱም የሥራና የትምህርት ቋንቋ አማርኛ ብቻ እንዲሆን ተደረገ፡፡ ሌላው ጉዳይ ባለስልጣናት ሃይማኖትን ወይም አገርን ከዱ ተብለው ከሥልጣን እንዲነሡ ተደርገው ታሠሩ፣ ተገደሉ፣ ወይ በእስር ቤት እንዲሞቱ ተደረጉ፡፡ ይህን በተመለከተ የልጅ ኢያሱን ምሳሌ ብቻ ማንሳት ይበቃል፡፡

ጭቆናና አፈና ያንገፈገፈው ሕዝብ ባንድ በተወሰነ ደረጃ ላይ እምቢ በማለት በሥርዓቱ ላይ ማፈንገጡ (መሸፈቱ/revolt) አይቀሬ ስለነበረ በተለያዩ አካባቢዎች ለምሳሌ የራያ፣ የባሌ አርሶ አደሮች የትጥቅ ትግል ጀመሩ፡፡ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግን ችግሮቹን በአወንታዊ መልኩ ከመፍታት ይልቅ ትግሎቹን ለማቀጨጭ በአውሮፕላን በሞብ ሳይቀር በጦርነት ዘመተባቸው ብዙ ሺ ሰዎች ተገደሉ፣ አካለ ጎደሎ ሆኑ ንብረቶች በእሳት ጋዩ፣ ተዘረፉ፡፡

በአውሮፓ ኢምፔሪያሊም መስፋፋት ጊዜ ኤርትራና ሱማሊያ በኢጣሊያኖች፣ በፈረንሳዮችና በእንግሊዞች በኮለኒ ተይዘው ቆይተው ከአውሮፓውያኑ አገዛዝ ነፃ ከወጡ በኋላ በኢትዮጵያ ሌላም ጥያቄ ማንሳት ጀመሩ፡፡ ኤርትራውያን ነፃ ወጥተው የራሳቸውን የውስጥ ጉዳይ በራሳቸው ለመወሰን ለመቻል የሚያመች ሁኔታ እንዲፈጠር የትጥቅ ትግል እስከማካሄድ የሄደ እንቅስቃሴ ጀመሩ፡፡ የንጉሡ መንግስት መልስ ግን የጦርነት ዘመቻ ነበር ስለ ኤርትራ ጦርነትና ስላስከተለው ጥፋት ሁሉም ስለሚያውቀው የሚታወቀውን እዚህ መድገም አያስፈልግም፡፡

በሶማሌ በኩልም የጥያቄው አቀራረብ ከኤርትራው ለየት ይበል እንጂ የሶማሌ ሕዝብ የራሱን እደል በራስ የመወሰን ጥያቄ ነው፡፡ የሱማሌ ሕዝብ አራት ሃይሎች አምስት ቦታ እንደቅርጫ አንደተከፋፈሉአት ማንም አይክድም (ጂቡቲ ሶማሌ - በፈረንሳይ፣ኦጋዴን ሶማሌ - በኢትዮጵያ ፣ ሰሜን ሶማሌ - በእንግሊዝ፣ ደቡብ ሶማሌ - በኢጣሊያን እና ኬንያ ሶማሌ - በእንግሊዝ) ፡፡ ሁለቱ ሶማሌዎች (ደቡብና ሰሜን) ነፃ ወጥተው ከተዋሃዱ በኋላ የተቀሩት ሶማሌዎችም ነፃ ወጥተው እንዲቀላቅሉአቸው ፈለገው ጥያቄ ማንሳት ብቻ ሰይሆን ከኢትዮጵያ ጋር ወደ ጦርነት ገቡ፡፡ በንጉሡ ዘመን በተከሰተው ጦርነት ምክንያት በሰው ህይወትና በንብረት ላይ የደረሰውን ጥፋትና ውድመት እናስታውሳለን፡፡

የንጉሣዊ አገዛዝ ለገዥ መደቡ፣ ለቢሮክራሲው ፣ ለፊውዳሊስቱና ለጥቂት ያገር ውስጥና የውጭ ባለሀብት ጥቅም የቆመ መንግሥት ነበር እንጂ የአገሩ የተፈጥሮና የሰው ሀብት ለልማት ውሎ ህዝቡ ከደህንነት ወጥቶ አገሪቱ የበለፀገች እንድትሆን ፍላጎት አልነበረም፡፡ ኋላቀርነት ድህነት በጥልቀት ተንሰራፍቶ ህዝቡ የምህበረ ኢኮኖሚ ችግሮችን ለመሸከም በማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር፡፡ የ1965/66 ዓ.ም ድርቅና የረሃብ አደጋ የዚህ ነፀብራቅ ነበር፡፡

በመሆኑም ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎችን የተረዱ ክፍሎች ማለትም የሠራዊቱ አባላት፣ ተማሪዎችና ምሁራን፣ አንዳንድ የሲቪክ ማህበራትና ጋዜጠኞች ሰለ ችግሩ ማንሳትና የተቃውሞ እርምጃዎች መውሰድ ጀመሩ፡፡ በዚያን ዘመን የፖለቲካ ፓርቲ ማቋቋም ቀርቶ የልማትና የእርዳታ መረዳጃ ማህበርን ማቋቋም እንኳ አይቻልም ነበር፡፡ ይህን ሁኔታ በተመለከተ የእነ መንግሥቱ ንዋይ መፈንቀለመንግሥት ሙከራና የተወሰዱት እርምጃ፣ የተማሪዎች ንቅናቄና በነሡ የተወሰዱ እርምጃዎች፣ በጋዜጠኞች መታሠርና በመጫ ቱለማ ማህበርና በአመራሩ ላይ የተወሰዱባቸውን እርምጃዎች ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡

በመጨረሻም መነሳት ያለበት ስለሰብኣዊና ዲሞክራሳዊ መብቶች መከብር ግንባር ቀደሞችን ነን ብለው የሚደነፉ የአሜሪካና የውሮፓ አገሮች በዘመናዊቱ ኢትዮጵያ አፈጣጠርና አጠባበቅ እንዲሁም በተከሰቱ የብሔርና የግለሰቦች መብት መጣስ ተጠያቂ ከመሆን የሚድኑ አይመስለኝም፡፤ ለራሳቸው ዓላማና ፍላጎት ሲሉ በአገራችን በታዩ ሁኔታዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋፅኦ አድርገዋልና፡፡

### 3.3 የብሔርና የግለሰብ መብት በደርግ ዘመን

እንደ ሌሎች መንግሥታት ሁሉ የደርግ መንግሥት የብሔርና የግለሰብ መብተ በገዢው ክፍል አመለካከት፣ ዓላማ መርህ ፖሊሲ እንዲሁም የፖሊሲው አፈፃፀም ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡

ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤት የነበረው ስከ 1987 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ጊዜአዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ነበር፡፤ በኋላ ብሔራዊ ሸንጎና ለስሙ ለሱ ተጠሪ የሆነ የመንግሥት ም/ቤት ሥልጣኑን ተጎናጽፎ፤ በተግባር ግን የሥልጣን ባለቤት ኢሠፓና ሊቀመንበሩ ነበሩ፡፡ የደርግና የኢሠፓ መንግሥት የስልጣን ምንጭ አምላክ ሳይሆን የመሳሪያ ሃይል ነበር፡፡ በዚህም ሃይል ፍላጎቶቻቸውን ያስፈጽሙ ነበር፡፡

የደርግና ኢሠፓ ዓለማ የሰፊው ጭቁን ህዝብ ወኪልነት “አብዮታዊት እናት ኢትዮጵያን“ መገንባት፣ መጠበቅና በኋላ ላይ ወደ ቅይጥ ኢኮኖሚ ቀየሩት እንጂ “ሶሻሊስት ኢትዮጵያን” መገንባት ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን ተልዕኮ ከግብ ለማድረስ የወል ግዳጅ ነበረባት፡፡

የሚቃወም ሁሉ አንደ ከሃዲ፣ እንደ የጭቁን ሰፊው ህዝብ ጠላት፣ አንደ ተገንጣይና አስገንጣይ፣ አንደ ፀረ አብዮተኛ፣ እንደ ኢምፔሪያሊስት ጥገኛና መልዕክተኛ ይታይና ይወገዝ፣ ይታሠር፣ ይገደል ነበር፡፡ በፀረ አብዮተኞችና ፀረ እናት አገር ላይ በሚካሄደው ጦርነት ላይ ሕዝቡ በሙሉ እዲታሠር የወል ግዳጅ ነበረበት፡፡

ደርግና ኢሠፓ አንደ ንጉሡ አይከሰሱም አይገሰሱም ነበር፡፤ የነሱ ደጋፊ፣ ጥገኛና ተቀጥላ ካልሆነ በስተቀር ሌሎች ተቃዋሚዎች እንዲኖሩ አይፈልጉም፡፡

ዘመቻ ተካሄዶባቸው ካገር ቤት እንዲጠፉ ተደርጓል፡፡ የተቃዋሚ መሪዎችና አባላት በሽዎች ታሥረዋል፣ ተገድለዋል፡፡ ሥልጣን ከመጠን በላይ የተማከለ ነበር ለምሳሌ ያህል የሁሉም የታች እርከን የአስተዳደር አካላት እቅዶች፣ በጀት፣ ሌሎችም ውሳኔዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት ብሔራዊ ሽንጎው ከጸደቀ በኋላ ነበር፡፡

እምነትን በተመለከተ ሁሉም ሃይማኖቶች በአድሃሪነት ይወገዙ ነበር፡፡ በተለይም የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በኢምፔሪያሊስዝም ወኪሊነት ይወገዙ ነበር፡፡ ቤተክርስቲያናቸው ተዘግተዋል፡፡

በኢኮኖሚ አንፃር የግል ንብረት የመያዝ መብት አልነበረም ሆኖም ግን ለዘመናት ተንሰራፍቶ የነበረው የፊውዳል የመሬት ሥርዓት ተገርስሶአል፡፡ ጥያቄው መሬት ለአራሹ ሆኖ ነበር ወይስ አይደለም የሚለው ነው እንጂ አርሶ አደሩ ከፊውዳል ጭቆናና ብዝበዛ ተላቆአል፡፤ ሆኖም ግን አርሶአደሩ የላቡ ውጤት የሆነውን ምርት ለማህበረ ኢኮኖሚ ችግሮቹ መፍቻና ለብልፅግና ሊጠቀምበት አልቻለም ነበር፡፡ ጥሮ ግሮ ያገኛት ምርት ለደርግ ጦርነት ዘመቻ ጥቅም ላይ ይውል ነበር፡፡ የህብረተሰቡ አምራች ሃይል ወደ ጦር ሜዳ ሄዶ እንዲያልቅ ተደርጎ ነበር፡፡ ስለሆነም ደርግና ኢሠፓ ኢኮኖሚውን ከማልማት ይልቅ እንዲወድምና እንዳያድግ በማድረጋቸው በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች በድርቅና በረሃብ አደጋ እንዲያልቁ አድርገዋል፡፡

ደርግና ኢሠፓ ትኩረታቸው የእናት አገር ደህንነት፣ አብዮታዊ ሶሻሊስት እናት አገር መገንባት እና የሰፊው አርሶ አደር ሕዝብ ድልን መጠበቅ እንጂ የብሔሮችንና የግለሰቦችን መብቶች ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ ደንታ አልነበረውም፡፡ የ1987 (እ.እ.አ) ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 53 ይህን ጉዳይ በማንሳት ሁሉም ዜጋ የብሐራዊ ውትድርና መብትና ግዴታ እንዳለው ይደነግጋል፡፤

የብሐሮች መብት ጥያቄን በተመለከተ ደርግና ኢሠፓ እርግጥ

ሀ. ጥቂት ቋንቋዎች በሚዲያ ጥቅም እንዲውሉ

ለ. የብሐረሰቦች ጥናት ኢንስቲቲዩት እንዲከፈት

ሐ. 5 የራስ አስተዳደርና 24 የአስተዳደር አካባቢዎችን እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡

መ. የአካባቢዎቹ ብሔረሰቦች ቋንቋዎች ባህልና በጎ ልምዶች እንዲዳብር እንዲስፋፉና በጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ሙከራ ጀምረው ነበር፡፡

ሆኖም ግን ይህ ሁሉ ጥገናዊና ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ የሚጠቅሙ እንጂ የብሔረሰቦች መብቶች ጥያቄዎች በተገቢው ፖለቲካዊ መንገድ አልተመለሱም ነበር፡፡ በመሆኑም የብሔር መብት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ እንዲያገኙ ለምሳሌ በኤርትራ፣በትግራይ፣ በአማራ (ኢህድን) በኦሮሚያ በኦጋዴን፣ በደቡብ (ለምሳሌ ሲዳማ) በጋምቤላ ፣ ቤንሻንጉልና በአፋር ብሔር በነፃነት ድርጅቶች ተፈጥረው ለመብት ጥያቄዎ መመለስ ትጥቅ አንግበው ይታገሉ ነበር፡፡ ደርግና ኢሠፓ ግን ለመብት ጥያቄዎች ጆሮና አይን ለመስጠት አልፈለጉም፡፤ በአውዳሚ ጦርነታቸው ቀጠሉበት እንጂ፡-

የ1987 (እ.ኤ.አ) ሕገ መንግሥት አንዳንድ አንቀጾች ስለ ደርግ ባህሪይ ያሳዩናል፡፡ ለምሳሌ ያህል የህገ መንግስቱ 27 አንቀጾች ስለ መሰረታዊ የዜጎች መብቶ፣ ስለፖለቲካ መብቶችና ስለ ሰብአዊ መብቶች መከብር ያወሳሉ፡፡ እዛው በዛው ደግሞ ነፃ መሆን ያለበት ፍርድ ቤት በሸንጎው እንዲሚመረጥና እንደሚሻር የደነግጋል፡፡ ሸንጎውስ ምን ነበር? እንዴትስ ይመረጥ ነበር፡፡ የህገ መንግስት ተርጓሚ ሥልጣን የተሰጠው ለሸንጎው፣ ለመንግሥት ም/ቤትና ለዋና አቃቤ ሕግ ነበር፡፡ የሁሉም የበላይ ባለስልጣን ሊቀመንበሩ ነበር፡፡ እነዚህ የነዚህ አካላት ተሳታፊዎች የኢሠፓ አባላት አልበሩምን? ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጪ ብዙ ባለሥልጣናት አልተገደሉምን? ብዙ ሺ ወጣቶች እንዲፈጂ አልተደረገም ወይ ?

ስለደርግና ኢሠፓ መንግሥት ይህን ያህል ካልኩኝ በኋላ የደርግ ኢሠፓ አንደ ንጉሠ ነገሥቱ ሁሉ ለአላማቸውና ለጥቅማቸው ብለው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ይህንንም መንግሥት ሲረዱ የነበሩ የውጭ ሃይሎች አንደነበሩ እንዳይዘነጋ በማስታወስ ወደ የኢሕአዴግ ዘመን አልፋለሁ፡፡

### 3.4 የብሔርና የግለሰብ መብት ጥያቄ በኢህአዴግ ዘመን

የደርግ ኢሠፓ መንግሥት ወድቆ ኢህአዴግ ሥልጣን ከተቆናጠጠ እነሆ 18 ዓመት ሊሞላ አምስት ወራት ብቻ ይቀሩናል፡፡ የኢትዮጵያ ዜጎችና ሕዝቦች ለ17 ዓመታት ሰጣሱ የነበሩት የብሔርና የግለሰብ ሰብአዊ መብቶች ይከበራሉ የሚል ተስፋ ነበራቸው፡፡ እውነትም ኢህአዴግ ስልጣን እንደያዘ የታወጀው የሽግግር ቻርተር በክፍል አንድ አንቀጽ አንድና ሁለት የ(UN-Universal Declcaration of Human Rights ) የደገነገገውን የግለሰብና የብሔር ዲሞክራሲያዊ መብቶች በኢትዮጵያ እንደሚያከብሩ ይደነግጋል፡፡

በመቀጠልም በህዳር 29ቀን 1987 (እ.ኤ.አ) የፀደቀው የኢፌደሪ ሕገ መንግሥት እነዚህ መብቶች እንደሚከበሩ በ36 አንቀጾች በዝርዝር አስቀምጦታል፡፡ በተለይም በአንቀጽ 13/2 ላይ በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት መሰረታዊ የመብቶችና የነፃነቶች ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሠነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ፡፡ ብሎአል

ኢህአዴግም ራሱ በ1987 ዓ.ም አጽድቆ በበተነው ፕሮግራሙ

1. በህገ መንግሥቱ የሰፈኑትን የሠፊው ሕዝብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች <u>**ሳይሸራረፉ**</u> በተግባር ላይ እንዲውሉ እንደሚታገል፣
2. በሰፊው ህዝብ ቀጥተኛና ሰፊ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ መንግሥትን ለማቋቋም እንደሚሠራ፣
3. ለህገ መንግሥቱ የተከበረው የብሐየርና የብሄረሰብ ሕዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል ድረስ ያለ መብት <u>**ሳይሸራራፍ**</u> እንኪከበር እንደሚታገል፡፡
4. ለህገ መንግስቱ ተገዥ የሆነና ከፖለቲካዊ ድርጅት ቁጥጥር ነፃ የሆነ የመከላከያ ሰራዊትና የፖሊስ ሃይል ለመመስረትና ለማጠናከር እንደሚሠራ
5. ለህገ መንግሥቱ ተገዥና ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅቶችና የአስተዳደር አካላት ቁጥጥር ነፃ የሆነ ዲሞክራሳዊ ፍርድ ቤቶች እንዲገነቡ እንደሚታገል ቃል መግባቱን አውጆ ነበር፡፡

ዛሬ ግን ኢህአዴግ በነዚህና በሌሎችም ጉዳዮች ችግሮች አሉብህ ተብሎ ሲነገርና ሂስ ሲቀርብለት አፍህን ዝጋ! ዝም በል! ህዝብ መርጦኝ በም/ቤ አብላጫ ወንበር ስላገኘሁ በህገ መንግሥቱ መሰረት መንግሥት ያቋቋምኩት እኔ ስለሆንኩኝ የፈለግሁትን ሕግ አወጣለሁ፣ የፈለግሁትን አካል እንደፈልግሁ እዝበታለሁ፣ እንደፈለግሁ እሰራለታለሁ፡፡ ይለናል፡፡

በዚህ ጽሑፍ ሁሉን ማንሳት አይቻልም እንጂ ኢህአዴግ የራሱን ፕሮግራማዊ ቃል ኪዳን፣ ሕገ-መንግስቱንና ቻርተሩን የጣሰባቸውን ያፈረሰባቸውን ምሳሌዎች በማንሳት ኢህአዴግ

እንደፈለገ በመንቀሳቀሱና ብዙ ጥፋቶች በመፈጸሙ ምክንያት እውነት ሕገ-መንግሥቱ እያስከበርኩ ነኝ የሚል ሞራላዊ ብቃት አለው እንዳሌለው መከራከር ይቻላል፡፡

**ጥቂት ምሳሌዎችን ብቻ ላቅርብ**

የኢሕአዴግ መንግስት ሰዎችን በጥይት ቆልቶ፣"ፀጥታንና ሕገ መንግስትን ለማስከበር ነው ያደረግሁት፣ ፖሊስ ተልዕኮውን ተቀባይነት ባላቸው የፖሊስ ሥራ እንዲሠራ ለማስቻ የፖሊስ የትጥቅ እቃዎችን የምገዛበት ገንዘብ የለኝም ይለናል"፡፡ አጥፊዎች ወደ ፍርድ አያቀርብም፡፡

የብሔርና የግለሰቦች መብት በመጣስ ጥቃት የፈጸሙባቸው ብዙ ሰዎች ሕይወታቸውን ያጡበት ሁኔታ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በሸካ መጀንገር፣ በአዋሳ፣ በጋምቤላና በኦሮሚያ የተፈፀሙጽ ግድያዎች እናስታውሳለን፡፡

ዜጎች ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተይዘው ይታሰራሉ፡፡ ቤታቸው ይፈተሻል፣ ሕገ መንግሥቱ በሚያዘው መሠረት ወደ ፍርድ ቤት አይቀርቡም፣ በእስርም ላይ እያሉ መብቶቻቸው አይጠበቁም፣ ቶርችም ይደረጋሉ፣ ሰዎች ከታሰሩ በኂላ ገና መረጃዎች ይፈለጉባቸዋል፣ የዋስ መብት አይጠበቅላቸውም፣ ፍ/ቤት ነፃ ያወጣቸው ግለሰቦች በፖሊስ ግብታዊነት በእስር እንዲቆዩ ይደረጋል፣ ብዙ ሺህ ዜጎች ያለፍትህ ለዓመታት በእስር ቤት ታጉረው ይቀመጣሉ፡፡ በዚህም ፍትሕ "ያተንተተ ፍትህ ማጣት ነው" እንደተባለው ፍትህ ያጣሉ፡፡ ዜጎች ፀረ ልማት፣ ፀረ ህዝብ ፣ ፀረ ዲሞክራሲያዊ የሕዝቦች አንድነት፣ ጥገኞች፣ ኪራይ ሰብሳቢዎች፣ ጦርነት ናፋቂዎች፣ የሽብር ተግባርና ድርጅት ደጋፊዎች ወዘተ ተብለው ይወገዛሉ፡፡ በዚህም ብዙ ንፀሀን ዜጎች ታሥረዋል፣ አካለ ጎደሎ ሆነዋል፣ ከመኖሪያ አካባቢያቸው እንዲፈናቀሉና እንዲሰደዱ ተደርገዋል፡፡

በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 29 የተከበረው የአመለካከት እና ሃሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት በተግባር እየተከበረ አይደለም፡፤ አፋኝ የሆኑ የሚዲያ ህጎች ይወጣሉ፡፡ የአንቀጽ 29 ንዑስ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ እስከ አንቀጽ 6 የተደነገጉ መብቶች እየተከበረ አይደለም፡፡ የግል ኤሉክትሮኒክስ ሚዲያ አይፈቀድም ጋዜጠኞች ከሥራ ይባረራሉ፣ ይታሠራሉ፣ ብዙ ጋዜጦች ያለበቂ ምክንያት ፈቃድ ይወሰድባቸዋል፣ ፈቃድ አይታደስላቸውም፡፡

ከሕገ መንግስት ድንጋጌ ውጭ የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት ይከለክላ፡፡ የመደራጀት መብት ባለመከበሩ ምክንያት ከ1983 ጀምሮ እነ ኢሠአፓ፣ መኢሶን፣ ኦነግ እና አብነግ የመሳሰሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ካገር ውስጥ የፖለቲካ ሂደት ተሳትፎ ተገልለዋል፡፡

ኢህአዴግን የሚቃወሙ ሌሎች ድርጅቶች የጥገኛ የኪራይ ሰብሳቢ ወኪሎች ናቸው ወይም መሃል ሰፋሪዎች፣ ወላዋዮች ናቸው እየተባሉ ወይ እንደ ድርጅት እንዳይኖሩ ወይም የኢህአዴግ ተቀጥላ እንደሆኑ ይደረጋል፡፡ እንቅስቃሴዎቻቸው ይገደባል ወይም እንደበታተኑ ይደረጋል፡፤ ዲሞክራሲያዊና ነፃ ምርጫ የሚካሄድበት ሁኔታ አልተፈጠረም፡፡

ሌሎች ሊነሱ የሚገቡ ጉዳዮችም አሉ፡፡ የዜጎች መብቶችና ነፃነቶች እንዲረገጡ መንገድ የሚከፍትና በዚህም ምክንያት የዜጎች ሰብአዊ መብቶች የተጣሱበት ሕጎች ታውጀዋል፡፤ በምሳሌነት የሚጠቀሱት እንደ አዋጅ 255/94፣ በእና አቶ ሰዬ የዋስ መብት መከልከልን በተመለከተ የወጣ አዋጅ፣ የባንክ አዋጅ፣ እና የኪራይ ቤቶች አጀንሲ አዋጅ ናቸው፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት በሕገ መንግስቱ የተከበሩ መብቶችን የሚጥሱ እንደ ፕሬስ፣ ምርጫ ቦርድ፣ የፖለቲካ ሕጎች አውጥቶአል፡፡ ከነዚሁ ተርታ የሚመደብ የሲቪክ ማህበራትም በቅርቡ ይፀድቃል ተብሎ ይገመታሉ፡፡

የዜጎች የመኖርና የማህበራዊ ዋስትናን በተመለከተ ወደ ድህነት ተርታ የሚቆጥረው ሕዝብ በፍጥነት እየጨመረና እየሰፋ እያለ ያገራችን ኢኮኖሚ እያደገ ነው ይባላል፡፡ የድርቅና የረሃብ ችግር ሰፊ ሆኖ እያለና የሰዎች ህይወት በብዛት እየጠፋ እያለ ይህ የጠላቶች ፕሮፖጋንዳ ነው ይባላል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በዘመድ፣ በጉቦና በፖለቲካዊ ወገንተኝነት መሥራትና ሥልጣንን ለግል ጥቅም በመጠቀም መበልጸግ ሰፍቶአል፡፡ በክልሎችና በፌደራል መንግስታት ወይም ብሔሮች መካከል ያላው ሚዛናዊነት ከጥያቄ እየገባ ነው፡፡ በክልሎች መሃከልም እንዲሁ፡፡

በዚህች አገር የጋራ ሃብትን በፍትሃዊ መንገድ፤ የጋራ ሥልጣንን በፍትሐዊ መንገድ መካፈል አለ ወይ? ሕዝቦች ወይም ክልሎች በእርግጥ የራሳቸውን ጉዳይ በራስ እየወሰኑ የራሳቸውን ሀብት እየተጠቀሙ ራሳቸውን በራስ ያስተዳድራሉ ወይ የሚለው ጥያቄም መነሳት ያለበት ነው፡፡ የብሔር መብት ጥያቄ የሚያነሱ የፖለቲካ ድርጅቶች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ የኢህአዴግ መንግስት ግን እልኸኛና ግትር በመሆን ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ችግሮች እንዲደባበሱ፤ ግጭቶች እንዲቀጥሉ በማድረግ የብሔር መብት ጥያቄዎች ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ በሆነ የፖለቲካዊ መፍትሔ እንዲገኝ ከማድረግ ይልቅ አስገዳጅ ስልቶችን መርጦ እየሄደበት ነው፡፡በዚህም ምክንያት መስመማት ስላልተቻለ ግጭቶች ይከተላሉ፡፡ በግጭቶች ምክንያትም ችግሮቹ ባሉባቸው አካባቢዎች ንፁህን ዜጎች የግጭቶቹ ሰለባ ይሆናሉ፡፡ የመብት ጥያቄ የሚያነሱ ግለሰቦችም በጎሪጥ ይታያሉ ከሥራ ይፈናቀላሉ፣ ይታሠራሉ፡፡

ብዙ የመብት አንሺ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይጠረጠራሉ፣ ይታሠራሉ፡፡እንግዲህ ባጭሩ የብሔርና የግለሰብ መብት ሁኔታና ጥያቄ ይህን ይመስላል፡፡ ይህም ማለት የብሔርና የግለሰብ መብት በኢህአዴግ ዘመንም እንዳልተመለሰ ያሳየናል፡፡

በመሆኑም "መብት ተከብሮአል፣ ከዚህ የበለጠ ምን ፈልጋችሁ ነው የመብት ጥያቄ የምታነሱት" የሚሉና "የብሔርና የዜጎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶ ስለተመለሱ ስለነዚህ መብቶች ማንሳት ትተን ፊታችንን ወደ ኢኮኖሚ ልማት ጥያቄ እናዙር" የሚሉ አባባሎችና ፕሮፖጋንዳዎች ሳያዝናኑን ያለውን እውነታ በማየት ባገራችን እስካሁን ዘልቆ የመጣንና አሁንም ያለውን የብሔር እና የግለሰብ መብት ጥያቄ ባግባቡ የሚመለሱበት አቅጣጫ መቀየስ የግድ ይለናል፡፡

**4.ምን እናድርግ**

ችግሮችን መዘርዘር ቀላል ሲሆን ለችግሮቹ መፍትሔ መንገዶችን መጠቆም ግን እጅግ የሚከብድ ነው፡፤ ቢሆንም ሊሸከምና ሊወረውራት የሚችላትን ትንሽ ድንጋይ ብወረወር ትልቁን ጉድጓድ ለመሙላት አስተዋፅኦ ያደረጋልና አስቲ ከመፍትሔ አንፃር የምችላትን ያህል ልበል፡፡

1. ባገራችን መብቶች የሚነኩ ነባር አሉታዊ ባህሎችና ልምዶች አሉ፡፡ እነዚህ ባህሎችና ልምዶች አሁንም ቢሆን በአስተዳደጋችንና በእለት ተእለት እንቅስቃሴዎች ላይ ተፅእኖ ያሳድራሉ፡፡ ስለሆነም ባህሎቻችንና ልምዶቻችን በጥልቀት እየፈተሽን ማሻሻልና ከዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ደረጃ ጋር እንዲጣጣሙ ማድረግ ሃላፊነታችን ነው፡፤ አጠቃላይ ህብረተሰባችን፤ የሕዝብና የመንግስት ተቋማት፣ የፖለቲካ ድርጅቶ አባላትና አመራር እንዲሁም የመንግስት ባለ ስልጣናት በዚህ ረገድ ሊያስቡበትና የባሕርይ ለውጥ ሊያደርጉበት ይገባል፡፡
2. በሡልጣኔትም ሆነ በንጉሥ ሥርዓት የእግዚአብሔር ወይም የአላህ የመሃመድ በጎች ለመጠበቅ የተላክን ነን የሚሉ መሪዎች ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤት ሆነው ህዝቦቻቸውን እንደፈለጉ በጉልበት ይገዙ ነበር፡፡ በዚህም የግለሰቦችንና የሕዝቦችን መብቶች ይረግጡ ነበር፡፡

   ደርግና ኢሠፓ በሰፊው ሠርቶ አደር ወኪልነት፣ በአብዮታዊት እናት ኢትዮጵያ ጠባቂነት ራቸውን ሰይመው፣ የሶሻሊስት ዲሞክራሲን፣ ወይም የጭቁን ሠርቶ አደር አምባገነንነት ሥርዓት ለመገንባት በሃይል ገዝተዋል፡፡

   ኢህአዴግ በስልጣን ኮርቻ ላይ እስኪቆናጠጥ ድረስ፣ በላብ አደሩ መሪነት፣ በአርሶ አደሩ አጋርነት፣ በንኡስ ከበርቴው ሪዘርቭነትና በጭቁን ብሔሮች ድርጅቶች ትብብር ሳያቋርጥ ወደ ሶሻሊሽት ስርዓት የሚያሸጋግር ለዚህም ለም መሬት የሆነ ለሰፊው ጭቁን ህዝብ ጥቅም የሚቆም

ዲሞክራሲያዊ አብዮትን አካሄዳለሁ ይል ነበር፡፤ የዲሚክራሲያዊ አብዮት ጠላቶችን ለመደምሰስ የሚቻለው በሃይል ብቻ ነው ይል ነበር፡፡

ከ1983 እስከ 1993 ይህንን አላማውን በጠረጼዛ ስር በመደበቅ የሰፊው አርሶ አደር ፓርቲ መሆኑና ለአርሶ አደሩ ብቻ ቅድሚያ እንደሚሰጥ በዚህም ምክንያት የሌሎች የህብረተሰቡ ክፍሎች ወኪሎች ማግለል እንዳለበት አውጆ በዚሁ አቅጣጫ ሲንቀሳቀስ ነበር፡፡

ከ1993 ወዲህ ደግሞ መስመሩን በመቀየር የህብታም አርሶ አደርና የንዑስ ከበርቴ ዲሞክራሲን በመገንባት ላይ እንዳለ ኢህአዴግም የንዑስ ከበርቴ ፓርቲ መሆኑን፣ የሚገነባውም ሥርዓት የንዑስ ከበርቴ ዲሞክራሲ (የንዑስ ከበርቴ አምባገነንነት) ስለሆነ የሎሎች የህብረተሰቡ ክፍሎች፣ማለትም የደሃው ገበሬ፣ የሠራተኛውንና የክፍተኛውን ከበርቴ ወኪሎች ከቁጥጥር ሰር አስገብቶ የሱ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ እንዲነግስ (ልዕልና እንዲያገኝ) እየሠራ ነው፡፡

ግልፅ መሆን ያለበት ቁምነገር የሦሥቱም ሥርዓቶች ባህርይ የወልነት (collectiionist) ፍላጎትን (collective will) ማንገሥ ነው፡፡ በዚህ አይነት ሥርዓት የግለሰብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶ ዋጋ አይሰጣቸውም፡፡ ግለሰብ ለወል ፍላጎት መገዛት አለበት፡፡ ግለሰብ ለወል ፍላጎት (will and Interest) ካልተንበረከከ ከሃዲ ነው፣ አስፈላጊም ከሆነ የሃይል እርምጃም ይወሰድበታል፡፡ ሌላው ጉዳይ ሦስቱም የሥርአቶቹ መሪዎች ለኢትዮጵያ አንድነት የቆምን ነን ይላሉ፡፡ የንጉሰ ነገሥቱን መንግሥት ነፃነትና አንድነት እንጠብቃለን፣ አብዮታዊት እናት ኢትዮጵያን በደማችን እንጠብቃታለን፣ አንድ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አገር እንፈጥራለን፣ የህዝቦች ዲሞክራሲያዊ አንድነት አንጠብቃለን በማለት ይደነፋሉ፡፡ ነገር ግን ለብሔርና ለግለሰብ መብት ጥያቄ ደንታ የላቸውም በዚህም የአገሪቱ ደህንነት፣ አንድነት፣ ሉአላዊነት ነፃነት አደጋ ላይ ጥሰዋል እየጣሱም ናቸው፡፡

የማህበረ ኢኮኖሚያዊ ዓላማችንን በተመለከተ፣ የግለሰብ ሰብአዊና ዲሚክራሲያዊ መብቶ በተመለከተ የብሔር መብት ጥያቄ አመላለስን በተመለከተ፣ የተለያዩ ግለሰቦች ከእነ ኢህአዴግ የተለየ አስተሳሰብ ሳይኖራቸው አይቀርም፡፡ ከኢህአደግ ፕሮግራም የተለየ አማራጭም ያቀርባሉ፡፡ ጥያቄው ኢህአዴግ ስለፈለገ ብቻ ለዓላማቸው መታገል ይተው ወይ የሚል ነው? ለኔ መልሱ ኢህአዴግም ሆነ ሌሎች አስተሳሰባቸውና ዓላማቸውን ይቀይሩ ያለበለዚያ ይጥፉ የሚል አይደለም፡፡ ይልቁንም እኔ ብቻ የኔ ብቻ የሚሉ collectivist/Hegemonic አስተሳሰብ ቀርቶ የሕዝብ በነፃ ምርጫና በነፃ ህዝብ ውሳኔ የራሱን ምርጫ እንዲሰጥ ሁኔታን እናመቻችለት ነው፡፡ ድርጅቶች ይኑሩ፣ በነፃነት ይንቀሳቀሱ፣ ሕዝቡ ይወስን ፣ ድርጅቶች ፍላጎታቸውን በሌላውና በሕዝቡ ላይ አይጫኑ፡፡

3. **የብሔር መብትን በተመለከተ** አንድነትም ሆነ የብሔር መብት በተጓዳኝ መከበር ጠቃሚ ነው እንጂ ጉዳት የለመውም፡፤ በእኔ አመለካከት የሕገ-መንግሥት አንቀጽ 8 እና አንቀጽ 39 መኖር ችግር አያመጣም፡፡ የአንድነትም ሆነ ለብሔር መብት ተከራካሪዎች የሚያቀርቡአቸው የየራሳቸው መከራከሪያዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ዛሬም ሆነ ነገም ሁለቱ ላይታረቁ ይችላሉ፡፤ ቢዘህ አይነት ሁኔታ ፍርድ የሚሠጥ ዳኛ ያስፈልገናል፡፤ ይህም ዳኛ ሊሆን የሚችለው ህዝቡ ብቻ ነው፡፤ የፈለገውን ቡድን የመምረጥ የሕዝቡ መብት ይከበር፡፡ ይሻለኛል በሚላ አቅጣጫ ወይም ሀሳብ ላይ ህዝቡ ይወሰን፡፡
4. ይህ እንዳለ ሆኖ አንድነት ይሻለናል የሚሉ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ሊያስቡበት የሚገቡ አሠራሮችም አሉ፡፤ ለምሳሌ ያህል
   ሀ. የshared rule, Shared Resource, Self Rule, Self Resource መርሆዎች የሚፈጠሩበትን የውስጣዊ የራስን እድል በራስ የመወሰን (Internal Self-Determination) መርህ መከተልና መገንባት፡፡
   ለ. የፌደራልና የክልሎች ግንኙነት በተመለከተ ክልሎች ከሌሎች ክልሎችና ከፌደራል መንግስታት የሚደርሱባቸውን ተጽእኖና ጣልቃ መግባት ለመከላከል የveto እና የNallification መብት እንዲኖራቸው ማድረግ፣
   ሐ. በየክልሎች የግለሰቦችና የአናሳ ቡድኖች የሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ እንዲከበሩ ማድረግ ፣
5. ያገራችን የአሁኑ ትልቁ ችግር የክትትል፣ የቁጥጥርና የተጠያቂነት ሥርዓት መታጣት ነው፡፡ በመሆኑም የሥልጣን ሚዛን (Balance of Power) የቁጥጥርና የተጠያቂነት ሥርዓት የለም፡፡ በመሆኑም የሥልጣን ሚዘን (Balance of Power) የቁጥጥርና የተጠያቂነት ስለቶች የሚፈጠሩበት ሥርዓት መፍጠርና ማጠናከር አንገብጋቢ ነው፡፡
6. በUN-Declaration Of Human Rights ሙሉ በሙሉ እንዲከበር ሁሉም በፅናት እንዲታገል ይገባል፡፡ በተጨማሪም ሁሉም ዜጋ ካገሪቱ የጋራ ሀብት በፍትሐዊ መንገድ እንዲቋደስ የማሀብራዊ ዋስትና ስርዓትን መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡
7. ሕገ መንግሥት ከዚህ በላይ የተቀጠመጡትን ነጥቦችና ሌሎችን ጉዳዮች ከግንዛቤ በማስገባት በጥልቀት ተመርምሮ የማሻሻያ ሃሳብ እንዲቀርብ፣ ማሻሻያውም ሆነ አጠቃላይ ሕገ-መንግሥት ለሕዝብ ውሳኔ እንዲቀርብ መሥራት፡፡

## ዋቢ ሰነዶች


1. Aalen Lovise; Institionalizing the plicies of Ethinicity. Actors, Power and Mobilizaation in Southern Ethiopia Under Ethinic Fedralism፡ Department of Political Science, Faculty of Social Science, Univieristy of Oslo, 2008.
2. አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ መስያ እምነቶች: ነሐሴ 1989
3. አገራዊ ለውጦች፣ ቀጣይ ዲሞክራሲያዊ መፍትሔዎች፡ ሰኔ 2000 ዓ.ም
4. Allen Buchanan: Sucession : The Morality Of Plitical Divorce from Fort Sumter to Lithuenia: Qubec C. Boulder: West View Press, 1991.
5. Allessandro Trialzi; Sallt, Gold and Legitimacy, Prelude to the History of a No-mans Land, Bela Shangul, Wallagga, Ethiopia (Ca 1800-1898): Napoli; 1981
6. በቀለ ወልደማሪያም አዴሎ፡ የከፋ ህዝቦች እና መንግስት አጥር ታሪክ አዲስ አበባ 2004 (1996 ዓ.ም)
7. ዶክተር ላጲሶ ጌ.ድሌቦ፡ የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ አዲስ አበባ፣ 1982.
8. Bonnie K. Holcomb, Sisai Ibsa: The Invention of Ethiopia. The Red Sea Perss, New Jersey, 1990.
9. Edward Halleth Carr: The New Society Beacon Pess, Boston, 1969.
10. Heinrich Scholler: Ethiopian Constitutional Legal Development, Volume I: Essays on Ethiopian Constitutional Development፡ Ruediger Koeppe Verlag, Koeln, 2005.
11. International Tansparancy, Commission on Africa; Ethiopia, The political Economcy of Human Rights (n.d)
12. Letter In Amharic Addressed by the Emperor Menilik to the Powers in April, 1891.
13. Merera Gudina: Ethiopia Competing ethinic nationalisms and the quest for democracy, 1960 — 2000. 2003
14. ሜይ-ደይ: የኢትዮጵያ አብዮት ታክቲክና ስትራተጂ፣ ክፍል - 2 ቁ 8፣ የማሌሊት የውስጥ መፅሔት (ትረጉም በኢማሌህ፣ የካቲት 1981
15. Negasso Gidada: History of Sayyo Oromoo of Southern Wallaga, Ethiopia from About 1730 to 1886.

16. Ronald L. Watts: Comparing Federal Systems. Institute of Intergevornmental Relation. Queen's Univeristy of Kingston, Ontario, Canada, 1999.
17. የኢህአዴግ ፕሮግራም ለሃገር እድገትና ለጭቁኖች ጥቅም የቆመ ፕሮግራም ነው። ነሐሴ - 1981
18. Seyoum Y.Hameso, Trevour Truman, Temesgen M.Erenna: Ethiopia, conquest and Quest for Freedom and Democracy. TSC publication, London, 1997
19. የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግንባር (ኢህአዴግ) ፕሮግራም፣ 1987
20. የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር: ነጋሪት ጋዜጣ አምስተኛ ዓመት ቁጥር 1፣ አዲስ አበባ፣ ሐምሌ 15 ቀን 1983 ዓ.ም
21. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት ምክር ቤት: ሕዝባዊ ዓላማችን የተባበረ ጥረታችንን ይጠይቃል። መስከረም 28 ቀን 1980 አዲስ አበባ
22. Ghelawdewos Araia: Ethiopia, The Politial Economy of Transiton University Press of America, Inc., Lanham, New York, London, 1995.